# አዲስ ዘመን

እንድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 333 ነሐሴ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የጸጥታና ደኅንነት ሥራዎች አዎንታዊ ለውጥ ማምጣታቸው ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የጸጥታና ደኅንነት ሥራዎች የውስጥ ተጋላጭነትን በመቀነስ፣ ሀገራዊ ደኅንነትን ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ አዎንታዊ ለውጥ ማምጣታቸውን ብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤቱ ገለጸ።

የደኅንነት ምክር ቤቱ ትናንትና ሀገራዊ የደኅንነት ሁኔታውን መገምገሙን አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ችግር ፈቺና ተግዳሮቶችን የሚቀንሱ፣ ሰላምና ጸጥታን ለማስፈንና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎቻችንን ለማሳለጥ የሚረዱ ወሳኝ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል።

በኦሮሚያ ክልል ሸኔን ለመደምሰስ የሚያስችሉ የሸዋ፣ የወለጋ፣ የጉጂ ኮማንድ ፖስቶች መደራጀታቸውንና መከላከያ፣ የክልሉ አመራርና ጸጥታ ኃይሎች በጋራ የተቀናጀ ሥምሪት እያካሄዱ መሆኑን ጠቁሟል።

ሶስት ሺህ 180 የሸኔ ታጣቂዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውንና ሌሎች መደምሰሳቸው፣ በርካታ መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች፣ ገንዘብና ንብረቶች ከጠላት መማረካቸው በመግለጫው ተመላክቷል።

በጠላት ተይዘው ከነበሩ አንድ ሺህ 739 ቀበሌዎች መካከል አንድ ሺህ 255 ያህሉ እንደገና ተደራጅተዋል። በርካቶችም ወደቀያቸው መመለሳቸው ተጠቁሟል።

በተመሳሳይ በአማራ ክልል በተወሰደው የተቀናጀ ሥምሪት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተጠርጣሪዎች በሕግ ጥላ ሥር መዋላቸው ተገልጿል።

ከቅማንት ሕዝብ ጋር በተገናኘ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ተከስቶ የነበረውን ጸጥታ ችግር እንዳይባባስ ለማድረግ በውይይት

የጸጥታና ደኅንነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገት የባንኮች ድርሻ ከፍተኛ እንደነበር ተጠቆመ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት በውስብስብ ችግሮች ውስጥ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ላሳየው አበረታች እድገት የአገሪቱ ባንኮች ሚና ከፍተኛ እንደነበር የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ አስታወቀ። የዋጋ ግሽበቱ ፈተና እንደነበርም ጠቁመዋል።

ትናንት የአገሪቱ ባንኮች የ2014 ዓ.ም የሥራ አፈጻጸም በተገመገመበት ወቅት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ገዢ ዶክተር ይናገር ደሴ እንደተናገሩት፤ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ኢትዮጵያን ጨምሮ የአለም አገራት ኢኮኖሚ በኮሮና ወረርሽኝ፣ በጸጥታ ችግርና በራሺያና በዩክሬን ጦርነት ምክንያት ክፉኛ ተፈትኗል።

በዚህም የተነሳ የአንዳንድ አገራት ኢኮኖሚ የቁልቁለት ጉዞ በያዘበት ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አበረታች እድገት ማሳየቱ የሚደነቅና የሚያኮራ ውጤት እንደሆነም ዶክተር ይናገር ጠቁመዋል።

ለተመዘገው የኢኮኖሚ እድገት የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች የአንበሳ ድርሻ እንደነበራቸው የተናገሩት ዶ/ር ይናገር፣ ለእነዚህና ለሌሎች የልማት ዘርፎች እድገት የፋይናንስ አገልግሎት

ለተመዘገበው የኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - አዩብ ተፈራ

ዶክተር ይናገር ደሴ











## የአትሌቲክሱ ድል ዘርፈብዙ ትርጉም ያለው አኩሪ ተግባር መሆኑን አትሌት ስለሺ ስህን ተናገረ

ገጽ 4







# በክፍለ ከተማው 57 ፕሮጀክቶች ተመረቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በ459 ሚሊዮን ብር በጀት የተሰራውን ህንፃ ጨምሮ ነባርና በ60 ቀናት ተገንብተው የተጠናቀቁ የተለያዩ 57 ፕሮጀክቶች ተመረቁ።

በምረቃ ስነስርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፤ የከተማ አስተዳደሩ በ2014 ዓ.ም ከያዛቸው እቅዶች 334 ፕሮጀክቶችን በስኬት ማጠናቀቅ የቻለ ሲሆን፤ በህዝቡና በበጎ አድራጊ ባለሃብቶች ትብብር ደግሞ ሌሎች ከ300 በላይ ፕሮጀክቶች መስራት ተችሏል።

ፕሮጀክቶችን በመገንባት ሂደት ህዝቡ ከጎደሎው እያወጣ በየአካባቢው ተሳትፎ በማድረግ እየተጠናከረ መምጣቱ በእጅጉ የሚያኮራ ነው ብለዋል።

ቀደም ሲል "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" በሚል እሳቤ ብዙ ፕሮጀክቶችን ጀምረው ተጥለው የሄዱና የህዝብን ሃብት ያባከኑ መኖራቸውን የጠቀሱት ከንቲባ አዳነች፤ ነገር ግን እነኚህን በየአካባቢው የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ለቅመን የህዝብ ሃብት ስለሆኑ ልዩ ትኩረት ሰጥተን በመስራት አጠናቀን ለህዝብ ጥቅም አውለናል ብለዋል።


ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ህንፃ

አሁንም ከለውጥ በፊት የተጀመሩ ውላቸውን ለማቋረጥ እንኳን ያላገኘናቸው ኮንትራክተሮች አሉ ያሉት ከንቲባዋ፤ ሃገር የምትገነባው በጋራ በመሆኑና ፕሮጀክቶች ስንጨርስም የምንጠቀምበት በጋራ ስለሆነ እንዲህ የሚያደርጉ አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ አሳስበዋል። ባለሃብቶች የሚያድጉትም የሚለወጡትም ህዝብ በተገቢው አገልግሎት ሲያገኝ ነው ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

እነዚህ ፕሮጀክቶች ትርጉማቸው ብዙ ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ በክፍለከተማው ተቋማት በተለያየ ቦታ ተበታትነው አገልግሎት ሲሰጡ በመቆየታቸው ህዝቡ ሲጉላላ የነበረበት ሁኔታ ከመኖሩም ባሻገር ተቋማትም ለቢሮ ኪራይ ተዳርገው እንደነበር ጠቁመዋል።

በተመረቀው ፕሮጀክትም ህዝቡን አክብረን ልናገለግልበት ፤ ለህዝብ የገባነውን ቃል ልንተገብርበት ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

ለዚህ ፕሮጀክት ስኬት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ፕሮጀክቱ በተጓተተበት ጊዜ በመድረስ እና የጎደለውን በመሙላት ላደረገው አስተዋፅኦ ምስጋና አቅርበዋል።

በእለቱ ለምረቃ ከበቁ ፕሮጀክቶች ውስጥ የአድዋ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት፣ 9ኛው የምገባ ማዕከል፣ ፓርኮች፣ የክፍለ ከተማ የአስተዳደር ህንፃ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ማዕከላት፣ ሰባት ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የአደባባይ ማስዋብ ፕሮጀክቶች፣ የዳቦ ፋብሪካና መሸጫ ሱቆች እንደሚገኙበት ከከንቲባ ጽህፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# በ60 ቀናት ዕቅድ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች መታየታቸው ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የ60 ቀን ዕቅድ ይዘን ወደ ተግባር በመግባታችን የህዝብ የኑሮ ጫና በሚቀንሱ፤ ሰላምና ደህንነቱን በሚያረጋግጡ እና ልማት በሚያመጡ ስራዎች ተስፋ ሰጪና ለቀጣይ ስራችን አቅም የሚፈጥሩ ውጤቶችን ማየት ችለናል ሲሉ የብልፅግና ፓርቲ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ መለስ አለሙ ገለጹ።

ኃላፊው አቶ መለስ አለሙ ትናንት እንደገለጹት፤ ብልፅግና ፓርቲ የመጀመሪያውን ታሪካዊ ጉባዔ በማካሄድ ያስቀመጣቸውን ውሳኔዎችና ያመላከታቸውን አቅጣጫዎች ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማ በየደረጀው የህዝብ ውይይት በማድረግ የ90 ቀን ዕቅድ ተይዞ ወደ ተግባር ተገብቷል።



አቶ መለስ አለሙ የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ተዘዋውረው ጎብኝተዋል

የ90 ቀን ማርሽ ቀያሪ የሆነውን የ60 ቀን ዕቅድ ይዘን ወደ ተግባር በመግባታችን የህዝብን የኑሮ ጫና የሚቀንሱ፤ ሰላምና ደህንነቱን የሚያረጋግጡ፤ እና ልማት የሚያመጡ ስራዎችን በማከናወን ተስፋ ሰጪና ለቀጣይ ስራችን አቅም የሚፈጥሩ ውጤቶችን ማየት ችለናል ብለዋል።

የሃሳብ፣ የጊዜና የህዝብ አቅም ጥምረት የሚሰጠንን ትሩፋት በተግባር ያየንበት የ60 ቀናት ፍሬዎች ለቀጣይ ስራችን የፈጠሩልን አቅም ፋይዳቸው ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ መለስ፤ ይህ ውጤት የተገኘው ተጨማሪ በጀት፣ አዲስ እውቀትና ክህሎት እንዲሁም ቁስና ቴክኖሎጂ ተጨምሮ ብሎም ህግ ታውጆ ሳይሆን የአስተሳሰብ ለውጥ፣ የጊዜ አጠቃቀምና የህዝብ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ተግባቦት መሆኑን ገልጸዋል።

በተሰራው ስራም የነዋሪው ሰላሙ እንዳይናጋ፣ የኑሮ ጫና ወደከፋ ደረጃ እንዳይሸጋገር መደረጉን ጠቁመው፤ ከፊታችን ያለው ተስፋና ፈተናን ካየንና ከጨበጥነው በላይ የሚጠይቀን በመሆኑ በጊዜ አጠቃቀማችን ያገኘነውን ትምህርት በቁጭት ትምህርት በመውሰድ ዛሬን የበለጠ ለመጠቀም የስራ ባህላችንና የአመራር ዘይቤያችንን ባህል በማሻሻል ህዝብን የሚያረኩ ስራዎች በትጋት መስራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

ካለፈው ጥንካሬና እጥረት በመማር የጀመርናቸውን የልማት ስራዎች የማስቀጠልና አዳዲስ ፕሮጀክቶችንም በጊዜ ገደብ ሸንሽነን ለውጤት መረባረብ ቀጣይ ስራችን መሆን አለበት ያሉት አቶ መለስ፤ በዚህ መንፈስ እንቅስቃሴ ከተደረገባቸው ክፍለ ከተሞች መካከልም አንዱ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ነው ብለዋል።

ክፍለ ከተማው የተጀመሩትን ስራዎች በማፋጠን፣ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በመጀመር ከተከናወኑ ተግባራት መካካል ሪቫን መቁረጥ ጀምሯል ያሉት አቶ መለስ፤ ወደፊትም ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ መለስ ገለጻ፤ ፈተናዎች ምንም ቢበዙ በጋራ እያሸነፍን የምንሻገራቸው እንጂ ከብልፅግና ጉዟችን ሊገቱን የሚችሉ አይሆኑም። ይህንንም በተግባር ገጥመንና ተጋፍጠን አይተናል፤ በአንድነት ስንቆም ወደ መልካም እድል ተለውጠው የከፍታ ጉዟችን ጉልበት ይሆናሉ። ችግርና ፈተና ሆነው መታየታቸው እየቀረ በእለት ተእለት ህይወታችን እየተጋፈጥን የምናሸንፋቸው ናቸው።



# ለመኸር እርሻ ከ60 ሚሊየን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ የኬሚካል ግዢ ሊፈጸም ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በቀጣዩ የመኸር ምርት ዘመን የአግሮ ኬሚካል እጥረት እንዳይከሰት ከ60 ሚሊየን ዶላር በላይ በጀት ተመድቦ ግዥ ለመፈጸም እየተሰራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሶፊያ ካሳ እንደገለጹት፤ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተለይም የአግሮ ኬሚካል ግብአት ወሳኝነት አለው።

በመሆኑም በ2014/2015 የመኸር ወቅት የሚያስፈልገው የአግሮ ኪሚካል ግብዓት በክልሎች ፍላጎት መሰረት ቀደም ብሎ ግዥ መፈጸሙን ገልጸዋል።

ለተያዘው የመኸር ወቅት የአግሮ ኬሚካል እጥረት ሊገጥም ይችላል በሚል ስጋት በመንግስት ከ60 ሚሊየን ዶላር በላይ በጀት ተይዞ በግዥ ሂደት ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽንና በኦሮሚያ ፌዴሬሽን በኩል ግዥው እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፤ በአጭር ጊዜ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ይደረጋል ብለዋል።

በዘንድሮው የምርት ዘመን በዓለም አቀፍ ደረጃ የማዳበሪያ ዋጋ በመናሩ አይደርስም የሚል ስጋት የነበረ ቢሆንም፤ በቅንጅታዊ ስራ ከተገዛው 12 ነጥብ 8 ሚሊየን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ 96 በመቶው ሀገር ውስጥ ገብቶ መሰራጨቱንም ለኢዜአ ገልጸዋል።

ከቀናት በፊትም ለአርሶ አደሩ ቡቃያ ዕድገት የሚያገለግለው 50 ሺህ ቶን ዩሪያ ማዳበሪያ የጫነች መርከብ ጂቡቲ ደርሳ ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት ስራ እየተሰራ መሆኑም ተዘግቧል።

# ዳያስፖራው የገፅታ ግንባታና የዲፕሎማሲ ስራውን እንዲያስቀጥል ጥሪ ቀረበ

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- የዳያስፖራው ማህበረሰብ ባለፉት ዓመታት ለሃገሩ የገፅታ ግንባታና የዲፖሎማሲ ስራ ሲያደርግ የነበረውን በጎ ተግባር አጠናክሮ እንዲያስቀጥል የዳያስፖራ ኤጀንሲ ጥሪ አቀረበ።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሙሐመድ እንድሪስ ትናንት በሸራተን አዲስ ሆቴል በተካሄደው ሁለተኛው ከኢድ እስከ ኢድ መርሃግብር ላይ እንደገለጹት፤ የዳያስፖራ አባላት ኢትዮጵያ በነበረችበት አስቸጋሪ ሁኔታ ያበረከቱት የገፅታ ግንባታና የዲፖሎማሲ ስራ ከፍተኛ ስኬት የታየበት ነው።

እንደ ዶክተር ሙሐመድ ገለጻ፣ ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት አጣብቂኝ ውስጥ በነበረችበት ወቅት ችግሩን በመቀነስና በመቅረፍ ረገድ ትልቁን ድርሻ ተወጥተዋል። ይህን ተግባራቸውን በቀጣይነትም አጠናክረው እንዲያስቀጥሉና የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ሰላም፣ እድገት፣ ልማትና ብልጽግና ከዳር ለማድረስ በቀጣይም አገራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

በሁለት ዙሮች በመካሄድ ላይ ያሉት አገራዊ ጥሪዎች የየራሳቸው ዓላማን በመሰነቅ መካሄዳቸውን ያወሱት ዶክተር ሙሐመድ፣ በመጀመሪያው ዙር ከተከናወኑ ስራዎች መካከል ዲፕሎማሲያዊ ስኬቶችንና በሁለተኛው ዙር የገጽታ ግንባታ ስራዎች ማንሳት እንደሚቻል ጠቅሰዋል።

በሁለተኛው ዙርም ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶችን ተቀብላ በማስተናገድ ያላት አኩሪ ታሪክና በተለይም በእስልምና እምነት እድገት ውስጥ ያበረከተችውን አስተዋጽኦ የሚዘክሩ ሁነቶችን በማከናወን የገጽታ ግንባታ ስራዎችን ማሳደግ መቻሉንም ገልጸዋል።

ሁሉንም አገራዊ እሴቶችን በመጠቀም ኢትዮጵያ ከሃላል ኢንዱስትሪ የሚገባትን ድርሻ ማግኘት እንድትችል ዳያስፖራውና ሁሉም ኢትዮጵያውያን በመረባረብ ሊሰሩ ይገባቸዋል ብለዋል።

በመድረኩ ከተሳተፉ የሃይማኖት አባቶችም መካከል የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሀጂ ኢብራሂም ቱፋ በበኩላቸው፤ የሃላል ኢንዱስትሪን ከመጠቀም አንጻር ኢትዮጵያ ያላትን አንጻራዊ ተጠቃሚነት የሚያጎሉ ጉዳዮችን አንስተዋል።

በኢትዮጲያ ያሉትን እምቅ አቅሞች በመጠቀም በሃላል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለንን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ሁሉም ሊተባበር እንደሚገባም ፕሬዚዳንቱ አሳስበዋል።

የሃላል ኢንዱስትሪ ዓለም አቀፍ ገጽታና የደረሰበትን ደረጃ፣ ከኢንዱስትሪው ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች፣ በዘርፉ ያሉ መልካም ተሞክሮዎችና ለኢትዮጵያ የሚኖራቸው አንድምታ እንዲሁም ኢትዮጵያ በዘርፉ ለመጠቀም ያላት እምቅ አቅምን በተመለከተ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት እንደሚደረግባቸው አመላክተዋል።

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን በመድረኩ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፉ የሃላል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተደራሽነቷንና ተጠቃሚነቷን ለማሳደግ ባለድርሻ አካላት ሊረባረቡ ይገባል።

ኢትዮጵያ ለመካከለኛው ምስራቅ አገራት ካላት ቅርበትና ለአገራቱ ልታቀርባቸው ከምትችላቸው ምርትና አገልግሎቶች አንጻር እንዲሁም ከዓለም አቀፉ የሃላል ኢንዱስትሪ መጠቀም የሚያስችሏት በርካታ እድሎች እንዳሉም ጠቁመዋል።

ያለንን እምቅ አቅም በመጠቀም ተደራሽነትን ለማሳደግ በሁሉም ዓለማት የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎችና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ሊረባረቡ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያ የግብርና ምርቶችን ወደ መካከለኛው ምስራቅ አገራት በመላክ ላይ የምትገኝ መሆኗን ያወሱት ሚኒስትሩ፤ ምርቶቹን ለማቅረብ ካለን እምቅ አቅምና በአካባቢው ካለው ፍላጎት አንጻር በዘርፉ ብዙ መስራት ይጠበቅብናል ሲሉ ገልጸው፣ እንደ አገርም ገና ብዙ መስራት እንደሚጠበቅ አመላክተዋል።

የሃላል ኢንዱስትሪ ከግብርና ምርቶች በተጨማሪ በመድሀኒት፣ የመዋቢያ ግብዓቶችና አገልግሎት ዘርፎች ላይ ባለው ድርሻ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአራት ትሪሊዮን ዶላር በላይ የሚያንቀሳቅስ ዘርፍ እንደሆነ ጠቅሰው፣ ይህንን ሰፊ የገበያ አማራጭና አገራችን በዘርፉ ያሏትን እድሎች አሟጠን በመጠቀም በቀጣናውና በአለም ደረጃ የገበያ ድርሻችንን ለማሳደግ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሙሉ ሊንቀሳቀሱ ይገባል ብለዋል።

በሌላ በኩል በተከታታይ በተደረጉት አገራዊ ጥሪዎች በርካታ የዳያስፖራ አባላት ወደ አገር ቤት መምጣታቸውን የጠቆሙት የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ፤ የዳያስፖራው ወደ አገር ቤት በብዛት መምጣት በቱሪዝም ዘርፍ ተከስተው የነበሩ ጫናዎችን በማቃለል ረገድ አበርክቶው ከፍተኛ ነው ብለዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታና ከኢድ እስከ ኢድ ጉዞ ወደ አገር ቤት ብሔራዊ ኮሚቴ ጣምራ ሰብሳቢ አምባሳደር ብርትኳን አያኖ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት በመካሄድ ላይ ያሉ አገራዊ ጥሪዎች በርካታ አገራዊ ትሩፋቶችን አስገኝቷል ብለዋል።

ኢትዮጵያን ከሃላል ኢንዱስትሪ ጋር ከማስተዋወቅ ባለፈ ዘርፉን ከመጠቀም አንጻር ያሉንን እምቅ አቅሞች የምንረዳበትና የባለድርሻ አካላት ትስስር የሚፈጥሩበት ነው ሲሉም አምባሳደር ብርትኳን ተናግረዋል።

# የሶማሌ ክልል ወጣቶች ማንኛውንም ጠላት ስመመከት በተጠንቀቀ ላይ መሆናቸውን አረጋገጡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሶማሌ ክልል ወጣቶች የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን ሰላምና መረጋጋት ለማደፍረስ የሚሞክርን ማንኛውም ጠላት ለመመከት በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸውን ገለጹ። የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ ሙሀመድና ሌሎች የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ከክልሉ ወጣቶች ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይተዋል፡፡

በጅግጅጋ ከተማ የተካሄደው ውይይት ዓላማ የክልሉ ወጣቶች በወቅታዊ ሀገራዊና ክልላዊ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

ወጣቶቹ ከሰላምና ፀጥታ ጋር በተያያዘ ባለ 4 ነጥብ የአቋም መግለጫ በማውጣት ውይይታቸውን አጠናቅቀዋል።

ወጣቶቹ በአቋም መግለጫቸው ከሀገሪቱና ከክልሉ ፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር እና በቅንጅት ለመስራት ቃል ገብተዋል።

የክልሉ መንግሥትና የፀጥታ ኃይሎች ወራሪና አሸባሪውን የአልሸባብ ቡድን ለመከላከልና ለማጥፋት ስልታዊና የተቀናጀ ዘመቻ በማካሄድ የሰጡትን ምላሽ አድንቀዋል።

አሸባሪዎች በሀገሪቱና በክልሉ ላይ የቃጡትን ሙከራና የፈፀሙትን የፈሪ ጥቃት አውግዘዋል፡፡

ወጣቱ የህዝቡን ሰላምና መረጋጋት ለማደፍረስ የሚሞክሩ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ከመንግሥት ጋር በመሆን እንዲከላከል ጥሪ አቅርበዋል።

በመድረኩ ከርዕሰ መስተዳድር ሙስጠፌ ሙሀመድ በተጨማሪ ሌሎች የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች መገኘታቸውን የሶማሌ ክልል መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ መረጃ ያመለክታል።

# የቱሪዝም ዘርፉን ለማነቃቃት በበይነ መረብ የታገዘ ሥራ እየተሠራ ነው

## - የቱሪዝምና ቴክኖሎጂ ሳምንት ከነሐሴ 4 ጀምሮ ይካሄዳል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በኮቪድ ወረርሽኝ የተጎዳውን የቱሪዝም ዘርፍ እንዲያገግም ለማስቻል እና ለማነቃቃት በበይነ መረብ የታገዘ የማስተዋወቅና የማዘመን ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ገለፀ። የኦሮሚያ ክልል የቱሪዝምና ቴክኖሎጂ ሳምንት ከነሐሴ 4 ጀምሮ ለአራት ቀናት እንደሚካሄድም ተጠቁሟል።

የኦሮሚያ ክልል ቱሪዝም ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ነጋ ወዳጆ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንደገለፁት፤ በኮቪድና በሌሎች ችግሮች የተጎዳውን ሀገራዊ እና ክልላዊ ቱሪዝምን ለማነቃቃት ብሎም ለማዘመን በማኅበራዊ ሚዲያዎች እና በበይነ መረብ የታገዙ ማስታወቂያዎች እንዲሁም በመተግበሪያዎች አማካኝነት ዘርፉን በማዘመን ለማነቃቃት እየተሠራ ነው።

አቶ ነጋ በኮቪድ ወረርሽኝ አማካኝነት የዓለም ኢኮኖሚ መናጋቱን ተናግረው፤ ኦሮሚያ ክልልም የዚህ ገፈት ቀማሽ መሆኑን ጠቁመዋል። ይህንን የተቀዛቀዘ የቱሪዝም ዘርፍ ለማነቃቃት አሠራሮችን ማዘመንና ዲጂታላይዝ ማድረግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

በቱሪዝም ዘርፉ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን ዲጂታላይዜሽንን ወደሥራ እያስገባን ነው ያሉት አቶ ነጋ፤ ጎብኚዎችን ጨምሮ በቱሪዝም ዘርፉ ያሉ ተዋንያን በበይነ መረብ ያላቸውን ሃሳብ መስጠት የሚችሉበት ሥርዓት ተገንብቶ ወደ ሥራ ገብቷል ብለዋል።



አቶ ነጋ ወዳጆ

ምክትል ኮሚሽነሩ፤ የሰለጠነው ዓለም ቱሪዝሙ ላይ በወረርሽኙ የደረሰበትን ጉዳት በይነ መረብንና ዲጅታላይዜሽንን ተጠቅሞ እንዲያገግም እያደረገ መሆኑን ገልፀው፤ ኢትዮጵያ እንደ አንድ የዓለም አካል የቱሪዝም ዘርፏ በወረርሽኙ ተጎድቷል። ከጉዳቱ ማገገም የሚቻለው በበይነ መረብ በመጠቀም በምናስተላልፈው የቱሪዝም መስህብ መልዕክት ጎብኚዎችን መሳብ ስንችል እና ቱሪስቶች ሲመጡም ምቹ ሁኔታዎችን ስንፈጥር ነው ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ አቶ ነጋ ገለፃ፣ በተለይ የዲጂታል ሚዲያውን በመጠቀም በገበያ ልማት ዘርፍ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በተለያዩ የማህበራዊ ዘርፎች ‘ቪዚት ኦሮሚያ’ በሚል ስያሜ በበይነ መረብና ማኅበራዊ ሚዲያዎች የተለቀቁ የፎቶና የቪዲዮ የቱሪዝም መስህቦች ከ100 ሚሊየን በላይ እይታ አግኝተዋል።

በተጨማሪም የክልሉ የቱሪዝም ኮሚሽን፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን የማስፋት ኃላፊነት እንደተጣለበት የተናገሩት አቶ ነጋ፤ የባሌ የመዳረሻ ቦታ ልማት ዲዛይን መጠናቀቁን አስታውቀዋል። ሥራው በቅንጅት የሚሠራ በመሆኑ የመንገድ እና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን መገንባት በቱሪዝም ተቋም በኩል የሚሠራ ባለመሆኑ የንድፍ ሥራውን በማጠናቀቅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወደ ተግባር ለመግባት ዝግጁ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ በክልሉ ከነበሩ የቱሪዝም መዳረሻዎች በተጨማሪ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ 25 ተጨማሪ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ከተለያዩ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር ጥናት በማካሄድ ተጨማሪ የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲኖሩ መደረጉን አመልክተዋል።

በምሥራቅ አፍሪካ የመጀመሪያው የወይን ቱሪዝም በኦሮሚያ ክልል ባቱ ከተማ ላይ በሚገኘው ትልቅ የወይን ፋብሪካ እንዳስጀመሩም ገልፀዋል።

የፊታችን ዕሮብ በአዲስ አበባ ከተማ ስካይላይት ሆቴል የሚጀመረው የኦሮሚያ የቱሪዝም ሳምንት የቱሪዝም ቴክኖሎጂ ኢንኩቬሽን ማዕከላት ጉብኝት፣ የፓናል ውይይት፣ የፎቶና ቪዲዮ ኤግዚቢሽን እና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ይከበራል ብለዋል።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማልማት፣ የገበያ ልማት እና የማስታወቂያ ሥራዎች፣ የወዳጅነትና የሀብት ማሰባሰብ ሥራ እንዲሁም የጥናትና ምርምር እና የዳታና ዲጂታላይዜሽን ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ በቅርቡ የተቋቋመ ተቋም ነው።



አትሌት ስለሺ ስህን

# የአትሌቲክሱ ድል ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያለው አኩሪ ተግባር መሆኑን አትሌት ስለሺ ስህን ተናገረ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የአትሌቲክሱ ድል እንደ ሃገር ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያለው አኩሪ ተግባር መሆኑን አትሌት ስለሺ ስህን ተናገረ። በ19ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በተመዘገበው ድል የተሰማውን ደስታ በመግለፅ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብም የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክቱን አስተላልፏል።

አትሌት ስለሺ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፀው፤ ሀገራችን ባለችበት ነባራዊ ሁኔታ ላይ የአትሌቶቹ ማሸነፍ ዘርፈ ብዙ አንድምታ ያለው አኩሪ ተግባር ነው፤ ችግሮች እንኳን ቢኖሩ ችግርን ተቋቁሞ ሀገርን ማስቀደም ተገቢ ነውም ብሏል።

ድሉ ሀገራችን ካለችበት አጣብቂኝ አንፃር አስደሳችና አኩሪ ተግባር ነው ያለው አትሌት ስለሺ፤ በአትሌቶቹ መሀል ያለው የመረዳዳት፣ የመተጋገዝና ሀገርን የማስቀደም ስራ በሌላው ሀገር ላይ የሀገራችንን ሰንደቅ በኩራት እንድንሰቅልና በዓለም አደባባዮች አንገታችንን ቀና አድርገን ለመታየት አስችሎናልም ሲል ነው የተናገረው።

በየትኛውም የስፖርት ውድድሮች ላይ መተጋገዝና አብሮ መስራት የግድ መሆኑን የገለፀው አትሌት ስለሺ፤ የአትሌቶቹን ድል በየትኛውም የስራ ዘርፍ ላይ ተደማምጦ በመተባበር አንድ ላይ በመቆም መድገም እንደሚያስፈልግና ሀገርን ወደፊት ማራመድ እንደሚገባም ነው ጨምሮ የገለጸው።

በቀጣይ ዓመታት ላሉት የዓለም ዋንጫና የኦሎምፒክ ውድድሮች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የአሁኑን ብርታታቸውን ማስቀጠል እንደሚገባቸው የጠቆመው አትሌት ስለሺ፤ አንድነትና መተጋገዝን ልምድ ለማድረግም በቂ ልምምድ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ሁላችንንም የሚያስደስተው የድል ውጤት ቋሚ ሆኖ እንዲቀጥል ጠንክሮ መስራት እንደሚያሻም ነው ያመለከተው።

አትሌት ስለሺ ኢትዮጵያ ባለችበት ሁኔታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በ19ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ባስመዘገቡት ድል የተሰማውን ደስታ በመግለፅ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብም የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክቱንም አስተላልፏል።

በኮሎምቢያ ካሊ ከሀምሌ 25 እስከ 30 በተደረገው በ19ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ 6 ወርቅ ▯ 5 ብር እና አንድ የነሃስ በአጠቃላይ 12 ሜዳልያዎችን በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚ ከዓለም ሀገራት መሀል ደግሞ 3ኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን ማጠናቀቋ የሚታወስ ነው።

# ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በአግባቡ ለመሰብሰብ ዘርፉን በእውቀትና በቁርጠኝነት መምራት እንደሚገባ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሰመራ፡- ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በአግባቡ ለመሰብሰብ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ዘርፉን በእውቀትና በቁርጠኝነት መምራት እንደሚገባቸው የአፋር ክልል ርእሰ-መስተዳድር አቶ አወል አርባ አስገነዘቡ። በክልሉ በ2014 የገቢ አሰባሰብ እቅድ አፈጻጸምና የ2015 በጀት አመት እቅድ በተመለከተ ከወረዳ አመራሮች ጋር በሰመራ ከተማ ምክክር ተካሂዷል።

የክልሉ ርእሰ መስተዳድር አቶ አወል አርባ በመድረኩ ላይ እንዳሉት፤ በክልሉ ኢኮኖሚው የሚያመነጫቸው የተለያዩ የገቢ አማራጮች አሉ።

ይሁንና እስካሁን በክልሉ እየተሰበሰበ ያለው ገቢ በዋናነት ከስራ ግብርና ከጨው ምርት እንዲሁም ከሚታወቁ የገቢ አርእስቶች እንደሆነ ተናግረዋል።

በተለይም የህብረተሰቡ የኢኮኖሚ መሠረት ከሆነው የቁም እንስሳትና የመሬት መጠቀሚያ ግብርን ጨምሮ የማዘጋጃ ቤትና ተያያዥ የገቢ አማራጮች ላይ ትኩረት በመስጠት መሰብሰብ እንደሚገባ



አቶ አወል አርባ

አመልክተዋል።

ለተግባራዊነቱም በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ዘርፉን በእውቀትና በቁርጠኝነት ከፊት ሆኖ መምራት ተቀዳሚ ተልእኳቸው አድርገው መውሰድ እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ መሀመድ ሀሰን በበኩላቸው፤ የክልሉ መንግስት ለውጡን ተከትሎ የገቢ ሴክተሩ ላይ ባከናወነው ተቋማዊ የሪፎርም ስራዎች ከ800 ሚሊዮን ብር አልፎ የማያውቀው ክልላዊ ገቢ ባለፉት አራት አመታት ከ2 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን አመልክተዋል።

በዓመታቱ የገቢ አሰባሰቡ ከ270 በመቶ በላይ እድገት ማሳየቱን ጠቁመው፤ ይሁንና በክልሉ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ገቢ የመሰብሰብ አቅም አኳያ ብዙ የሚቀረው መሆኑን ጠቁመዋል።

ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ በክልሉ በ2015 በጀት አመት ከ3 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ለመሰብሰብ እቅድ መያዙን አመላክተዋል። ለመሰብሰብ የታቀደው ገቢ በ2014 በጀት አመት ከተሰበሰበው ከ41 በመቶ በላይ ጭማሪ እንዳለው ጠቅሰዋል።

"እቅዱን ለማሳካት በዋናነት ታችኛው መዋቅር ላይ የሚገኘው አመራር ዘርፉን የህልውና ጉዳይ አድርጎ በኃላፊነት መምራት ይጠበቅበታል" ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# የጸጥታና ደኅንነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የታገዘ መግባባት መፈጠሩን ምክር ቤቱ ጠቁሞ፣ በአጠቃላይ በክልሉ 633 አመራሮችና ባለሙያዎች ላይ ርምጃ መወሰዱ ተመላክቷል።

በአዲስ አበባ ከተማ የሕዝብን ጸጥታና ደኅንነት ከማረጋገጥ አንጻር መልካም ተግባራት መከናወናቸውን ምክር ቤቱ መገምገሙም ተገልጿል።

እንደ መግለጫው፤ በመዲናዋ ከ497 በላይ ሰዎች ከሽብር ጋር በተገናኙ በቁጥጥር ሥር ውለዋል። ለሽብር የተዘጋጁ የተለያዩ ሰነዶችና ዕቃዎችም ተገኝተዋል። የተደራጁ ወንጀሎችን ሲመሩ የነበሩ 314 ተጠርጣሪዎች ተይዘዋል። የከተማና የፌዴራል መንግሥት 75 የሥራ ኃላፊዎች በሙስና ተጠርጥረው ተይዘዋል። ከመሬት ወረራ ጋር በተያያዘ አንድ ሺህ 596 ቦታዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል። ይሁንና በመዲናዋ የፍትሕ አካላትን ከማጥራት አንጻር በበቂ ሁኔታ እንዳልተሠራ ተገምግሟል።

በሌላ በኩል በቤኒሻንጉል ጉምዝ ያለው የሥጋት ሁኔታ እየተሻሻለ መምጣቱንና ከጠላት ነጻ ከወጡ 180 ቀበሌዎች መካከል በ169ኙ የመንግሥት መዋቅር መልሶ መደራጀታቸውን ምክር ቤቱ ገልጿል።

በደቡብ ክልል እየተከናወነ የሚገኘው ሰላምንና ደኅንነትን የማረጋገጥ ሥራ የተሻለ ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን የደኅንነት ምክር ቤቱ አስታውቋል።

ከብሔረሰቦች የሚነሡ የአደረጃጀት ጥያቄዎችን የመለየትና ጥያቄዎችን በሕጋዊ መንገድ ለመፍታት ጥረት በመደረጉ በኢ. መደበኛነት ተደራጅቶ ጫና የሚፈጥር ኃይል ወደ ሰላማዊ ሁኔታ እየተመለሰ መሆኑም ተጠቁሟል።

በሶማሌ ክልል ደግሞ ከውጭና ከውስጥ የሚመነጩ የደኅንነት ሥጋቶችን ለመከላከል፣ ለመቋቋምና ለማስወገድ ወሳኝ ተግባራት መከናወናቸው ተገልጿል።

በመግለጫው መሰረት፤ በክልል በተካሄደ ኦፕሬሽን 813 አሸባሪዎች ተገድለው 79 ተማርከዋል። በርካታ የጦር መሣሪያዎች ተማርከዋል። በሂደት የሀገር መከላከያ ሠራዊት የተሳተፈበት ኮማንድ ፖስት ተቋቁሟል።

በአፋር ክልልም የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር ከመስራት ባለፈ ዋናውን የኢትዮ-ጂቡቲ መሥመር ደኅንነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ሥራ መሠራቱንና ከአጎራባች ክልሎች ጋር በመነጋገር የጸጥታ ችግሮችን ለመፍታት እየተሞከረ መሆኑን ምክር ቤቱ ጠቁሟል።

በሌላ በኩል በትግራይ ክልል ያለው ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ መንግሥት ቁርጠኛ መሆኑን ምክር ቤቱ አስታውሶ፤ በአካባቢው ያለውን የሥጋት ሁኔታም ከጸጥታ አካላት አቅም በታች መሆኑንና በተገቢው መንገድ ክትትል እየተደረገበት እንደሚገኝ ማረጋገጡን አስታውቋል።

እንደአጠቃላይ ሲታይ ሥራዎች ገና አለመጠናቀቃቸውን፤ የጸጥታና ደኅንነት መዋቅሩ በሚጠበቀው መጠን አለመጥራቱን፤ የአመራሩንና የሕዝቡን የጸና ሥነ ልቡና የመገንባት ሥራ በተገቢው ልክ አለመሠራቱን፤ ጁንታው ከውስጥና ከውጭ ኃይሎች ጋር ሊያደርገው የሚፈልገውን ቅንጅት በማምከን በኩል አለመሠራቱን በመግለጫው ተመላክቷል።

እነዚህ ጉዳዮች በተገቢው ትኩረትና ቁርጠኝነት ካልተሠሩ የተገኘው አንጻራዊ ሰላም ዘላቂ እንደማይሆን መገምገሙንና ቀሪ ሥራዎች በአመራር፣ በጸጥታ አካላትና በሕዝቡ ቁርጠኝነትና መሥዋዕትነት ሊተገበሩ እንደሚገባ ምክር ቤቱ አቅጣጫ አስቀምጧል።

# ስተመዘገበው የኢኮኖሚ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከማቅረብ አኳያ የባንኮች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ ሁሉም ያላሰለሰ ጥረት በማድረጉ በበጀት ዓመቱ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በመጨመር ከዘርፉ ብቻ ከ4 ነጥብ 2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ መገኘቱን የጠቆሙት ገዢው፣ በሐዋላ አገልግሎትና በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት አኳያም እድገት መመዝገቡን አንስተዋል።

በአገራችን በብዙ መመዘኛ የባንኮች ቁመና የተሻለ ደረጃ ላይ መሆኑን የተናገሩት ዶ/ር ይናገር፣ የባንክ አገልግሎት እስከታች የገጠርና ጠረፋማ አካባቢዎች ተደራሽነት ለማስፋት በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ብዙ ርቀት መሄድ መቻሉን ጠቁመዋል።

እንደ ዶ/ር ይናገር ማብራሪያ፣ ባንኮቹ ዘመናዊ የዲጂታል አገልግሎት ለመስጠት ባደረጉት እንቅስቃሴ በበጀት ዓመቱ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ደንበኞችን 43 ነጥብ 3 ሚሊዮን አድርሰዋል።

በዚህም የተከናወነው ግብይት 1 ነጥብ 16 ትሪሊዮን ብር እንደሆነና በሞባይል ባንኪንግ ብቻ 24 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ዝውውር እንደተደረገ የጠቆሙት ዶክተር ይናገር፤ 197 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ጥሬ ገንዘብ በኤቲ. ኤም ወጪ ተደርጓል ብለዋል። በአሁኑ ጊዜም የሞባይል ባንኪንግ ተጠቃሚዎች ቁጥር 16 ነጥብ 3 ሚሊዮን፣ የኤቲ.ኤም ማሽን ቁጥርም 6 ሺህ 902 ደርሷል ብለዋል።

በዘርፉ ስርቆት፣ በተለያዩ ስሞች የሚፈጸም ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ ፈተና እንደነበር ያስተወሱት ዶ/ር ይናገር ፣ መንግስት ችግሩን ለመቅረፍ ብር ከመቀየር ጀምሮ የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ እንደነበረና በቀጣይም ከዚህ አንጻር ሁሉም ባንኮች ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስበዋል።

የአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት በበለጠ ቀጣይነት እንዲኖረው ባንኮቹ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ ያሉት ዶ/ር ይናገር፣ በአገሪቱ 67 ሚሊዮን የሚሆነውን የሞባይል ተጠቃሚ ህዝብ የዲጂታል አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ በቁርጠኝነት እንደሚሰራ አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ በወጣቶቿ ዳግም አሸንፋለች!

ወጣቶች አፍላ ጉልበትና ክህሎታቸውን ለመልካም ሲጠቀሙበት አገር አሻጋሪ፣ ትውልድንም አኩሪ ታላቅ ስራን እንደሚሰሩ፤ በአንጻሩ ይሄ ትኩስ ሃይልና አቅም ለእኩይ ዓላማ ሲውልም አገርን ወደ ከፋ ችግር፣ ሕዝብንም ወደ መከራ እንደሚከት በርካቶች በሃሳብም፣ በጽሑፍም ሲተርኩ ይታያል፡፡ ይሄ እውነት ግን ከብሂልም በላይ በገሃድ በኢትዮጵያ ውስጥ በመንታ ገጽነት ሲገለጽ ኖሯል፡፡ እየተገለጠም ይገኛል፡፡ የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ ለዚህም የእናት ጡት ነካሽ ቡድንና ትውልድን ያፈሩና በሰው ደም የሰከሩ እንደ ሕወሓት አይነት ቡድኖችን በአንድ በኩል፤ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በልባቸው ከትበው ይሄን የልባቸውን ክታብ በዓለም አደባባይ ከፍ አድርጎ ለማንገስ በፈጸሙት ተጋድሎ ትውልድን በአንድ አሰልፈው የደስታ እንባ ሲያራጩና ሃሴትን ሲያጎናጽፉ የሚታዩ በርካታ የየሙያ ዘርፉ አርበኞችን በሌላው ገጽ ማየቱ በቂ ነው፡፡

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ዋጋ ከፍለው፤ ኢትዮጵያን አዘለቁ፤ ኢትዮጵያዊነትንም በትውልዱ ልብ አኖሩ፡፡ ይሄ የአበው ገድልና የታላቅነት ጉዞ በትውልዶች ቅብብሎሽ ደምቆ ከአውደ ውጊያ እስከ ዓለምአቀፍ የስፖርት መድረክ ሰንደቋን ከፍ ያደረጉ ተተኪዎችን ሳያጣ ዛሬም ድረስ ዘልቋል፡፡ ኢትዮጵያን ከወራሪ ነጻ ያደረገው ትውልድ፤ የኢኮኖሚ ነጻነቷን ለማወጅ የዘመናት የአባቶቹን ሕልም እውን ያደረገበትን ግድብ በዓባይ ላይ ገነባ፡፡ ስንዴ የመለመን ገጹን ለመቀየርም በግብርናው ዘርፍ በተለይም በስንዴ ልማት ላይ እጅ በአፍ ላይ እያስጫኒ ያለ ውጤትን ማስመዝገብ ጀመረ፡፡

ይሄ የአባቶቹን ታሪክ ያልዘነጋ ትውልድ መልካም ተግባር እንዲጠብቅ ሆኖ ግን፤ የወጣትነት አቅምና ሃይላቸውን ለመልካም ሳይሆን ለእኩይ ዓላማ ማስፈጸሚያነት ያዋሉ ጥቂት ወጣቶች የመሰረቱ ሕወሓት እና መሰሎቹን የሚዘውሩ ኃይሎች ግን ዛሬም ኢትዮጵያን ለመበተን፤ ኢትዮጵያውያንን ለማጎሳቆል ያላቸውን እኩይ ዓላማ ለማሳካት በዙሪያቸው ያሉ ወጣቶችን አሰባስበው ከመባዘን አልተቆጠቡም፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያን ገጿን ለማጠልሸት፤ ኢትዮጵያውያንንም አንገት ለማስደፋት በእጅጉ ከሚለፉ ዓለምአቀፍ ተቋማትና ሚዲያዎች ሳይቀር በእጅጉ የተለፋበት የሴረኞች ፍላጎት ጭምር ነበር፡፡ ይሁን እና ይሄን መጥፎ ጥላ ከኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያዊነት ላይ ለማንሳት የሚታትሩ እልፍ የኢትዮጵያ ልጆች ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነትን ዳግም ለመግለጥ የሚያስችላቸውን መድረክ ትናንት በአሜሪካ ኦሪገን፤ ዛሬ ደግሞ በኮሎምቢያ ካሊ አገኙ፡፡

እናም ኢትዮጵያ አበቃላት፣ በውስጥ ተከፋፍላ በጦርነት እየታመሰች፣ በሌሎችም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች እየተናጠች ናት፤ እናም ሕዝቧ አንድነት ርቆት መተባበር በማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል በተባለበት ወቅት፤ ኢትዮጵያውያን ወርቆች፤ “ኢትዮጵያ ዛሬም ታላቅ ናት፣ ኢትዮጵያውያንም እንደ ጥንቱ አብረው የቆሙ ኃያል ህዝቦች ናቸው፤ ለዚህ ደግሞ እዚህ ያለነው እኛ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ህያው ምስክሮች ነን” ሲሉ በአሜሪካዋ ኦሪገን ላይ በወርቅ፣ በብርና በነሃሳቸው ድል ኢትዮጵያን ከሃያላኑ አገራት በላይ ከፍ አድርገው አኑረው አሳዩ፡፡ ኢትዮጵያም በድላቸው አሸንፋ ከፍ አለች፤ ኢትዮጵያውያንም በወርቆቻቸው ወርቅ ተግባር፤ በአገራቸውም አሸናፊነት አደባባይ ወጥተው ድላቸውን በደስታ አጣጣሙ፡፡

የኦሪገኑ ድልና ከፍታ ከኢትዮጵያውያን ልብ ሳይወጣ፤ ከዓለም ዓደባባይ ከፍታው ሳይወርድ፤ ዛሬ ደግሞ የቀደምቶቻቸው ተተኪ የሆኑት ወጣቶች በኮሎምቢያ ካሊ መድረክ ላይ ነገሱ፡፡ ኢትዮጵያ ሲነኳት የምትበረታ፣ ሲፈትኗት፣ የምትጠነክር፣ ሊበትኗት ሲለፉ የበለጠ የምትሰባሰብና የምትተሳሰር መሆኗን በድጋሚ አረጋገጡ፡፡ በስድስት ቀን የመድረኩ ቆይታቸውም ስድስት ወርቅ፣ አምስት ብር እና አንድ ነሃስን በአንገታቸው አጥልቀው ኢትዮጵያንና ሰንደቋን በዓለም አደባባይ ከፍ አድርገው አሳዩ፡፡ በተለይ በውድድሩ ማጠናቀቂያ ዕለት በአንድ ሌሊት ያውም አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አራት ወርቅ እና ሁለት ብር የተገኘበት ሂደት የማይዘነጋ ከመሆኑ በላይ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ አራት ጊዜ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከየትኛውም አገር በላይ ከፍ ብሎ እንዲሰቀል፤ አራት ግዜም የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር በድል እንዲዘመር አድርገዋል፡፡

በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሄን መሰል የዓለም መድረክ በተደጋጋሚ ድሎች አሸንፋ የወጣችው ኢትዮጵያ፤ ጠላቶቿን መቅጣትና አንገት ማስደፋት ብቻ ሳይሆን፤ የቁርጥ ቀን ልጆቿንና ጀግኖቿን ማወደስና መሸለም፣ ከፍ አድርጋ ማሳየትም ችላበታለች፡፡ የኦሪገኑን ልዑክና ወርቅ ልጆቿን የተቀበለችበትና የሸለመችበት ሂደትም የዚህ አንዱ ማሳያ ሲሆን፤ በሕልውናዋ ላይ የዘመተባትን እኩይ አጥፊ ኃይል አይቀጡ ቅጣት የቀጡላትን ጀግኖች ልጆቿን ያሞገሰችበትና እውቅና ሰጥታ የሸለመችበት ሁነትም የቅርብ ትዝታ ነው፡፡

ይህ የኢትዮጵያዊነት ከፍታ ከኢትዮጵያ አመስጋኝ የእናትነት ባህሪ ጋር ተዳምሮም ነው ኢትዮጵያ በየዘመናቱ ከፍታዋን የሚያውጁ፤ አሸናፊነቷን የሚገልጡ ተተኪ ጀግኖችን ያላሳጣት፡፡ ከዚህም በላይ ኢትዮጵያዊነት የገባቸው፣ ስለ ኢትዮጵያ ግድ የሚላቸው ወጣት ተተኪዎቿ ከኦሪገኑ ደማቅ ድል ተምረው በካሊ አሸናፊነቷን አውጀዋል፡፡

ይህ የወጣቶቹ ድል ደግሞ በየዘርፉ ለተሰማሩ ወጣቶች አሸናፊነት ምን ማለት እንደሆነ፤ ኃላፊነትን መወጣት ዋጋው እስከምን እንደሆነ አስተምረዋል፡፡ በመሆኑም መድረኩ በአንድ በኩል ኢትዮጵያ ዳግም በተተኪዎቿ ያሸነፈችበት፤ በሌላ በኩል ሌሎች ወጣቶችና ወጣቶቹን የሚመሩ አካላት ከዚህ ድል ምን መማር እንዳለባቸው የቤት ሥራ የሰጠ ሆኗል፡፡ የካሊ ተሳታፊ ተተኪ ወጣቶችም አገር አሸናፊ አድርገዋልና ክብር ይገባቸዋል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ወጣቶችን ለመሪነት የማዘጋጀት መልካም ጅምር

ይበል ካሳ

ሁለቱ የፕላኔታችን ትልልቅ ክፍለ ዓለማት እስያና አፍሪካ በቆዳ ስፋታቸው ብቻ ሳይሆን በሕዝብ ብዛታቸውም ስድሳ በመቶ የሚጠጋው የዓለማችን ሕዝብ የሚኖርባቸው ግዙፍ አህጉራት ናቸው፡፡ እስያ ብቻ 41 ነጥብ 84 በመቶ የሚሆነውን የዓለማችን ሕዝብ የሚያዋጣ ሲሆን፤ አፍሪካ ደግሞ 17 ነጥብ 20 የሚሆነውን ድርሻ በመያዝ የሁለተኝነቱን ደረጃ ትይዛለች፡፡ ይህም ማለት በቀሪዎቹ አምስት አህጉራት ያለው የሕዝብ ቁጥር አንድ ላይ ተደምሮ በእስያና በአፍሪካ ብቻ ከሚገኘው የሕዝብ ቁጥር በሃያ በመቶ ያነሰ ነው እንደማለት ነው፡፡

የወጣቶችን ቁጥር በተመለከተም እንደዚሁ በድምሩ ከዓለማችን ወጣት የሕዝብ ቁጥር 80 ነጥብ 7 የሚሆነውን ድርሻ በመያዝ ሁለቱ ግዙፍ አህጉራት እስያና አፍሪካ በተመሳሳይ ከፊት ይቀመጣሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ 58 በመቶው የእስያ ሲሆን 22 ነጥብ 7 በመቶው ደግሞ ስድሳ በመቶ የሚሆነው ሕዝቧ ከሃያ አምስት ዓመት በታች፣ ከሲሶ በላይ የሚሆነው ሕዝቧ በ15 እና በ34 ዓመት ዕድሜ መካከል የሚገኝባትና እስከ ሰባ በመቶ የሚሆነው የሕዝብ ቁጥሯ በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝባትና “ወጣቷ አህጉር” በመባል የምትታወቀው የእኛዋ አፍሪካ ናት፡፡

ይህም ሁለቱ ግዙፍ አህጉራት በአግባቡ ከተጠቀሙበት ከራሳቸው አልፈው ዓለሙን ሙሉ ሊለውጡበት የሚችሉበት ወጣትነትን የሚያክል የዓለማችንን ግዙፍ ኃይል ጠቅልለው መያዛቸውን ያመላክታል፡፡ ሆኖም “የዓባይን ልጅ ውሃ ጠማው” እንዲሉ አበው እንደአለመታደል ሆኖ ይህ ሁሉ የዕድገትና የለውጥ ኃይል ባለበት እስያና አፍሪካ አብዛኛው ሕዝባቸው ዛሬም ከድህነት አረንቋ ያልተላቀቀባቸው የሃብታም ድሃ አህጉራት ናቸው፡፡ ያም ሆኖ በእምቁ የአህጉራቱ ሃብትና በግዙፉ የዕድገትና የለውጥ ኃይል፤ በወጣትነት ላይ በአግባቡ ከተሠራና ኢንቨስት ከተደረገ ዛሬም የማደግና የመበልጸግ ዕድሉ አለ፡፡

ለዚህም ግማሽ ክፍለ ዘመን ባልሞላ ጊዜያት ውስጥ የዓለምን ኢኮኖሚና ፖለቲካ እንደ አዲስ አፍርሶ እየሠራ የሚገኝ አስደማሚ ዕድገትና ልዕለ ኃያል የኃይል ሚዛን መፍጠር የቻሉት እንደቻይና ዓይነቶቹ አገራት ማሳያዎች ናቸው፡፡ ሌላዋ እስያዊት የግዙፍ የሰው ሃብት ባለቤት ሕንድም ወደዚህ ጎዳና እመጣች ነው፡፡ ከአፍሪካም አገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ እንደ ናይጀሪያ የመሳሰሉ በርካታ አገራት ይህ ዕድል አላቸው፡፡ ይህንኑ ለማድረግ

**የወጣቶች የትብብር መድረክ ብቁ አገር ተረካቢ ተተኪ አመራሮችን ለማፍራት ትልቅ ዕድል የሚፈጥርና ግዙፎቹ አህጉራት ያላቸውን ግዙፍ የዕድገትና የለውጥ የወጣትነት ኃይል በአግባቡ ለመጠቀምና ከቆዳ ስፋታቸውና ከሕዝብ ቁጥራቸው ጋር አብሮ የሚሄድ ግዙፍ አቅምና ኃይል ለመገንባት የሚያስችል ነውና ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል**

ግን ትልቅ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነትና አያሌ ኢንቨስትመንትን ይጠይቃል፡፡

ለዚህ ደግሞ ከአህጉራቱ መሪዎችና ከራሱ ከወጣቱ በርካታ ሥራ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ረገድ ዋና ዓላማውን ያላቸውን ግዙፍ የወጣት ኃይል በመጠቀም በሁለቱ ትልልቅ አህጉራት መካከል ትብብርንና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ ላይ አድርጎ በባለ ራዕይ ወጣት አፍሪካውያንና እስያውያን ወጣት መሪዎች አማካኝነት በአውሮፓውያኑ 2018 የተመሠረተው የአፍሪካ ኢስያ ወጣቶች ፎረም እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ አርዓያነት ያለው መልካም ጅምር ነው፡፡

ፎረሙ ዋና መቀመጫውን አፍሪካ ውስጥ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ በእስያ ደግሞ በታይላንድ ባንኮክ አድርጎ ባለፉት አራት ዓመታት መደበኛ ባልሆነ መንገድ የወጣቶችን አቅም የሚገነቡና ወደመሪነት የሚያመጡ በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን ከሰሞኑ ደግሞ “በአፍሪካና እስያ መካከል ቀጣይነት ያለው ዘላቂ ትብብርን ለማረጋገጥ የወጣቶች ሚና” በሚል መሪ ሃሳብ በመዲናችን አዲስ አበባ የመጀመሪያ መደበኛ ጉባኤውን አካሂዷል፡፡ ሰላም ግንባታ፣ ሥራ ፈጠራ፣ የወጣቶች መሪነትና ግብርና ላይም ዋነኛ አጀንዳዎቹ አድርጎ ተወያይቷል፡፡

በመድረኩ ላይ ከሦስት መቶ የሚበልጡ የሁለቱ ሃገራት ወጣቶች ተገናኝተው በተቀሱት አጀንዳዎች ላይ ተወያይተዋል፣ በተለያዩ ዘርፎች ላይም የልምድ ልውውጥ አድርገዋል፡፡ ወጣቶቹ ብቻ ሳይሆን ከሁለቱ አህጉራት የተውጣጡ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናትና ፖሊሲ አውጭዎች፣ ታዋቂ የሥራ ፈጠራና የፋይናንስ ዘርፉ አንቀሳቃሾች፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦችና ከሌሎች አህጉራት የተጋበዙ ወጣቶችና የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ መሪዎች ተገኝተው አፍሪካውያንና ኢስያውያን ወጣቶችን አዳምጠዋል፡፡ ወጣቶቹ ለአህጉሮቻቸውና ለመላው ዓለም ዘላቂ ልማት የልማትና የዕድገት አቅም መሆን የሚችሉበትን መንገድ በጋራ መክረዋል፡፡

በመድረኩ በስኬታማ መሪዎች ስብእናዎች፣ ፈጠራ የታከለበት አመራር፣ የወጣቶች በጎ ፈቃደኝነት፣ ራስን ማሳደግ በሚሉ ጉዳዮች ላይም ትኩረት አድርጎ የወጣቶችን ውሳኔ ሰጭነት ሚና ማሳደግ በሚቻልበትና የአገር ተረካቢ የሆኑትን ወጣቶች ለአመራር ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያግዙ የዕውቀትና የክህሎት ትጥቆችን ማስጨበጥ ላይ ያለመ ውይይም ተካሂዷል፡፡ በአንድ ወቅት የጀኔራል ኤሌክትሪክ ሊቀመንበርና ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበረው ታዋቂው አሜሪካዊ መሃንዲስ፣ ደራሲና የቢዝነስ ባለሙያ ጃክ ዌልች ነው እንዳለው መሪ ከመሆን በፊት ስኬት ማለት ራስን ለማሳደግ የምናከናውነው ማንኛውም ተግባር ነው፤ መሪ ከሆንን በኋላ ደግሞ ስኬት የሚባለው ሌሎችን ለማሳደግ የምንሠራው ማንኛውም ሥራ ነው፡፡

ስለሆነም የተፈጠረውን ዕድል በመጠቀም ወጣቶች ራሳቸውን በዕውቀትና በቴክኖሎጂ በማብቃት ብሎም በመልካም ሥነ ምግባር በማነጽ መሪነትን ከራሳቸው መጀመር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚያም አገራቸውንና አህጉራቸውን ለማልማትና ለመምራት ይቻላቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ እንዲህ ዓይነቱ የወጣቶች የትብብር መድረክ ብቁ አገር ተረካቢ ተተኪ አመራሮችን ለማፍራት ትልቅ ዕድል የሚፈጥርና ግዙፎቹ አህጉራት ያላቸውን ግዙፍ የዕድገትና የለውጥ የወጣትነት ኃይል በአግባቡ ለመጠቀምና ከቆዳ ስፋታቸውና ከሕዝብ ቁጥራቸው ጋር አብሮ የሚሄድ ግዙፍ አቅምና ኃይል ለመገንባት የሚያስችል ነውና ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል እንላለን፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# በወቅታዊ አገራዊ የደህንነትና ፀጥታ ጉዳዮች ዙሪያ በመምከር፣ ከብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት የተሰጠ መግለጫ

## "በእያንዳንዱ አካባቢ የሚከናወነው ጸጥታንና ደኅንነትን የማረጋገጥ ተግባር የመላዋ ኢትዮጵያ ሰላም የሚያጸና መሆኑን ማመን ያስፈልጋል"

- የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት

### የተከበራችሁ የአገራችን ሕዝቦች፣

ብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት ዛሬ ባደረገው ስብሰባ አገራዊ የደኅንነት ሁኔታ የገመገመ ሲሆን፣ በቀደሙት ወራት ተለይተው የነበሩ አገራዊ ሥጋቶችን መሠረት በማድረግ የተከናወኑ ተግባራትንና ያጋጠሙ ውስንነቶችን ለግምገማው መነሻ አድርጓል።

የደኅንነት ምክር ቤቱ ሰኔ 1 ባካሄደው ስብሰባው ወቅት በአስቸኳይ ለማከናወን ተወስነው ከነበሩ ተግባራት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

1. አሸባሪና የታጠቁ ቡድኖችን በአመራራቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ለመደምሰስ፣

2. ለጠላት ዐቅም የሚሆነው ከዳተኛ የጸጥታ ኃይል ስለሆነ፣ የዚህን ምክንያት፣ መነሻና ዋና ዋና ተዋንያን ለመለየት፣

3. ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እያወያዩ፣ በዓላማና በተግባር ላይ እየተግባቡ፣ የጋራ ተግባርን ለማቀናጀትና ግጭቶችን ትርምስ አልባ ወደሚሆኑበት መጠን ለመቀነስ፣

4. የሥጋት መነሻና የሥጋት ተዋንያን የሆኑ አካላትን ለማወያየትና ራሳቸውን ከሥጋት መነሻነትና ከሥጋት ተዋናይነት እንዲነጥሉ ለማድረግ፣

5. የተፈናቀሉ ዜጎችን ወደቀድሞ አካባቢያቸው በመመለስ ለማቋቋም፤ የፈረሱ የመንግሥት መዋቅሮችን መልሶ ለማደራጀትና ሥራ እንዲጀምሩ ለማድረግ፣

6. ኮንትሮባንድ፣ የኢኮኖሚ አሻጥር፣ ግድያ፣ ዝርፊያ፣ ኢመደበኛ አደረጃጀት፣ ወዘተ. ዓይነት ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎችን ከሥራቸው ነቅሎ ለማስቆም፣

7. የፍትሕና የጸጥታ ተቋማትን ለማስተካከል አቅጣጫዎች ተቀምጠው ነበር።

እነዚህን አቅጣጫዎች መሠረት በማድረግ የተከናወኑ ተግባራትን የተመለከተው የደኅንነት ምክር ቤቱ እጅግ ወሳኝ፣ ችግር ፈቺ፣ ተግዳሮቶችን የሚቀንሱ፣ ሰላምና ጸጥታን ለማስፈንና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎቻችንን ለማሳለጥ የሚጠቅሙ ተግባራት በክልሎችና በፌዴራል ደረጃ እየተከናወኑ መሆኑን አድንቋል።

በኦሮሚያ ክልል ሸኔን ለመደምሰስ የሚያስችሉ የሸዋ፣ የወለጋ፣ የጉጂ ኮማንድ ፖስቶች የተደራጁ ሲሆን፤ መከላከያ፣ የክልሉ አመራርና የክልሉ የጸጥታ ኃይሎች በጋራ የተቀናጀ ሥምሪት እያካሄዱ ይገኛሉ።

በዚህም 3180 የሸኔ ታጣቂዎች በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሲሆን እጃቸውን ላለመስጠት አሻፈረኝ ያሉት ተደምስሰዋል።

በተጨማሪም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአባ ቶርቤ፣ የአልሸባብና የጁንታው ሴሎችና ተባባሪዎች ተይዘዋል።

በኦፕሬሽኑ በርካታ የነፍስ ወከፍና የቡድን መሣሪያዎች፣ ተተኳሾች፣ ተሽከርካሪዎች፣ ገንዘብና ልዩ ልዩ ንብረቶች ከጠላት ተማርከዋል። በጠላት ተይዘውና ፈርሰው ከነበሩ 1,739 ቀበሌዎች መካከል 1,255 ያህሉ እንደገና ተደራጅተዋል። 252,129 የቤተሰብ አባላትን የያዙ 47,558 አባወራዎች ወደ ቀድሞ ቀያቸው ተመልሰዋል።

በተመሳሳይ በአማራ ክልል ሕግን ለማስከበር በተወሰደው የተቀናጀ የጸጥታ ኃይሎች፣ የአመራሩና የሕዝቡ ሥምሪት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተጠርጣሪዎች በሕግ ጥላ ሥር ውለዋል።

ከእነዚህ መካከል ገሚሱ የጸጥታ ኃይሎችን በመክዳት ለሕገ ወጥ ታጣቂዎች ዐቅም ሲፈጥሩ የቆዩ ሲሆኑ፣ የተቀሩት በልዩ ልዩ ወንጀሎች ሲፈለጉ የከረሙ ናቸው።

ከወያኔ ጋር ወግነው በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦችን እርስ በእርስ ለማጋጨት የሚሰሩ ታጣቂዎች ላይ ርምጃ የተወሰደ ሲሆን፣ ጠላት ተጨማሪ ሰው የማያገኙበት ደረጃ ላይ ለማድረስ እየተሠራ ነው። ከቅማንት ሕዝብ ጋር በተገናኘ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ተከስቶ የነበረውን ጸጥታ ችግር እንዳይባባስ ለማድረግ የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተው የተሻለ መግባባት ተፈጥሯል።

በአጠቃላይ በክልሉ እስካሁን ድረስ ከ6.6 ሚልዮን በላይ ሕዝብ የተሳተፈባቸው የውይይት መድረኮች የተካሄዱ ሲሆን፣ በ633 አመራሮችና ባለሞያዎች ላይም ከመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ጀምሮ በሕግ ቁጥጥር ሥር እስከማዋል የደረሰ ርምጃ ተወስዷል።

በአዲስ አበባ ከተማ የሕዝብን ጸጥታና ደኅንነት ከማረጋገጥ አንጻር መልካም ተግባራት መከናወናቸውን የደኅንነት ምክር ቤቱ በግምገማው ተረድቷል። ከ497 በላይ የጁንታው፣ የሸኔ፣ የአልሸባብና ሌሎች አክራሪ ቡድኖች በቁጥጥር ሥር ውለዋል።

ከእነርሱም ጋር የጸጥታ ኃይሎች አልባሳት፣ ሐሰተኛ መታወቂያዎች፣ ማኅተሞች፣ ለሽብር ተግባር የተዘጋጁ ሰነዶች፣ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች፣ የጦር መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ ለአሸባሪዎች ሊላኩ የነበሩ ተንቀሳቃሽ ስልኮች እና የባንክ ደብተሮች አብረው በቁጥጥር ሥር ውለዋል።

የተደራጁ ወንጀሎችን ሲመሩ የነበሩ 314 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሲሆን፣ 75 ከተማና የፌዴራል መንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በሙስና ተጠርጥረው ተይዘዋል።

በመሬት ወረራ የተወሰዱ መሬቶችን ማስመለስ እና ሕገወጥ ግንባታ የተፈጸመባቸው በጥቅሉ በ1596 ቦታዎች ላይ እርምጃ መውሰድ ተችሏል።

በአዲስ አበባ የተሠራው ሥራ ውጤት ማምጣቱን የደኅንነት ምክር ቤቱ ያረጋገጠ ሲሆን፤ የፍትሕ አካላትን ከማጥራት አንጻር በበቂ ሁኔታ እንዳልተሠራ ገምግሟል።

በተጨማሪም በከተማዋ የሚደረጉ የሕዝብ ውይይቶች በበቂ መተማመን የፈጠሩ አለመሆናቸውን፤ በሽብር እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ከዚህ በላይ ማጋለጥና መቆጣጠር እንደሚገባ፤ ሙስናና የኢኮኖሚ አሻጥርን መልክ ለማስያዝ በሙሉ ኃይልና በቁርጠኝነት መሥራት እንደሚያስፈልግ ምክር ቤቱ አሥምሮባቸዋል።

በቤኒሻንጉል ጉምዝ ያለው የሥጋት ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ፣ ሰላምና ደኅንነት ይበልጥ እየተረጋገጠ መምጣቱን ብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤቱ ተመልክቷል። በክልሉ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሕገ ወጥ ታጣቂዎች የተደመሰሱ ሲሆን፣ 1,826 የሚደርሱ ታጣቂዎች በቁጥጥር ሥር ውለዋል። 749 ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያዎች እና 5,639 ተተኳሾች ከጠላት የተማረኩ ሲሆን፣ 9 ጀልባዎችና 65 የጠላት ካምፖችም ወድመዋል።

እጃቸውን በሰላም የሰጡ ሕገወጥ ታጣቂዎችን ወደ መደበኛ ሕይወት የማስገባት እንዲሁም፤ በከማሺና በመተከል ዞኖች 171,485 ተፈናቃዮችን የማቋቋም ሥራ ተሠርቷል። ከጠላት ነጻ ከወጡ 180 ቀበሌዎች መካከል በ169ኙ የመንግሥት መዋቅር መልሶ ተደራጅቷል። በክልሉ አንጻራዊ ሰላም መስፈኑን፣ የሽፍታ ቡድኖች ዐቅም መዳከሙን፣ ተፈናቃዮችን መልሶ የማቋቋም ተግባር እየተሻሻለ መሄዱን፣ የደኅንነት ምክር ቤቱ በአዎንታዊነት የገመገመ ሲሆን፣ በቀጣይ ሊከናወኑ የሚገቡ ያልተጠናቀቁ ተግባራት መኖራቸውንም አይቷል።

ከእነዚህም መካከል ከሸኔና ከጁንታው ጋር እየተቀናጀ በድንበር አካባቢ የሚንቀሳቀሰውን የሽፍታ ቡድን ሙሉ በሙሉ የመደምሰስ፤ የመንግሥትን መዋቅር መልሶ ወደ ሥራ የማስገባት፤ በሰላም የገቡትን ታጣቂዎች ወደ ሰላማዊ ሕይወት እንዲመለሱ የማቋቋም ተግባራት ይገኙበታል። የክልሉ አመራሮች፣ የጸጥታ ኃይሎችና ሕዝቡ እነዚህን ተግባራት በቀሪ ጊዜያት እንደሚያከናውኗቸው ምክር ቤቱ የጸና እምነቱ መሆኑን አመልክቷል።

በደቡብ ክልል እየተከናወነ የሚገኘው ሰላምንና ደኅንነትን የማረጋገጥ ሥራ ካለፉት የተሻለ ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን የደኅንነት ምክር ቤቱ ገምግሟል።

ከብሔረሰቦች የሚነሡ የአደረጃጀት ጥያቄዎችን የመለየትና ለአገርና ለሕዝብ ዘላቂ ጥቅም በሚያስገኝ መንገድ ለመፍታት እየተሠራ ነው። ጥያቄዎችን ለመፍታት የሚያስችል ሁኔታ በመፈጠሩ በኢመደበኛነት ተደራጅቶ ጫና የሚፈጥር ኃይል ወደ ሰላማዊ ሁኔታ እየተመሰለ ነው።

በአዋሳኝ አካባቢዎች የሚታየውን የሸኔ እንቅስቃሴ ከአጎራባች ክልሎች ጋር ተቀናጅቶ የማስወገድ፤ ከክልል መደራጀት ጋር የሚነሡ ጥያቄዎችንና ቅሬታዎችን አስቀድሞ በመለየት በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ማገዝ፤ የአከላለል ጥያቄዎችን ለሕገ ወጥ ተግባራት መጠቀሚያነት እንዳይውሉ ፍላጎት ያላቸው ተዋንያንን አስቀድሞ በመለየት ተገቢውን ርምጃ መውሰድ እንደሚገባ የደኅንነት ምክር ቤቱ አቅጣጫ ሰጥቷል።

በሶማሌ ክልል ከውጭና ከውስጥ የሚመነጩ የደኅንነት ሥጋቶችን ለመከላከል፣ ለመቋቋምና ለማስወገድ ወሳኝ ተግባራት መከናወናቸውን የደኅንነት ምክር ቤቱ በግምገማው አረጋግጧል።

ሐምሌ 14 ቀን በአፍዴር ዞን በባሬና ጎት ጎት ወረዳዎች ሠርጎ ለመግባት የሞከረውን የአልሸባብ ኃይል ተከታትሎ ለመደምሰስ የክልሉ ልዩ ኃይል ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።

የክልሉ አመራር ሕዝቡን በማንቃት፣ በማሳተፍና በማደራጀት ጠላትን ለመደምሰስ ትምህርት ሰጪ እንቅስቃሴ አድርጓል። በሂደት የአገር መከላከያ ሠራዊት የተሳተፈበት ኮማንድ ፖስት የተቋቋመ ሲሆን፣ በተካሄደ ኦፕሬሽን 813 አሸባሪዎች ተገድለው 79 ተማርከዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የጦር መሣሪያዎች፣ ተተኳሽ ጥይቶች፣ ፈንጂዎችና መገናኛ ሬዲዮኖች ተማርከዋል።

ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር የሥጋት መሥመሮችን በመለየት ኬላዎች እየተጠናከሩ ቢሆንም አሁንም ሕገ ወጥ ተግባሩን በሚገባ ለመቆጣጠር አለመቻሉን፤ በጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት የጎሳ መሪዎችና አመራሩ በሚገባቸው ልክ አለመንቀሳቀሳቸውን፤ በጸጥታ ሥምሪት አፈጻጸም ላይ የሚታዩት የዲሲፕሊን ግድፈቶች መኖራቸውን፤ የአልሸባብን ሥጋትን በማስወገድ የውስጥ ደኅንነትን ለማረጋገጥ አሁንም የሚቀሩ ሥራዎች መኖራቸውን የደኅንነት ምክር ቤቱ በግምገማው አመላክቷል።

በአፋር ክልል የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር እየተሠራ መሆኑን የደኅንነት ምክር ቤቱ የገመገመ ሲሆን፣ በተለይም ዋናውን የኢትዮ-ጂቡቲ መሥመር ደኅንነት በማረጋገጥ በኩል ወሳኝ ሥራ መሠራቱን፤ ከአጎራባች ክልሎች ጋር በመነጋገር የጸጥታ ችግሮችን ለመፍታት እየተሞከረ መሆኑን ምክር ቤቱ በአዎንታ ተቀብሎታል።

በአንጻሩ የጠላት እጅ የተጨመረበት የኮንትሮባንድ ንግድ አሠራሩን እየቀያየረ፣ አድማሱን እያሰፋ መምጣቱን፤ በጸጥታ ኃይሎች መካከል የቅንጅት ክፍተት መኖሩን፤ የጎሳ ግጭቶችን በኃላፊነት መንፈስ ለመፍታት የሚያስችል ሥራ በበቂ ሁኔታ አለመከናወኑን ምክር ቤቱ ገምግሟል። በመሆኑም በቀጣይ እነዚህ ወሳኝ ጉዳዮች ትኩረት አግኝተው፣ ተገቢ ውጤት ለማምጣት በሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጸሙ አቅጣጫ አስቀምጧል።

### ውድ ኢትዮጵያውያን፣

በትግራይ ክልል ያለው ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ በድርድር እንዲፈታ መንግሥት አቅጣጫ መያዙና የተግባር እንቅስቃሴ ማድረጉ የአደባባይ እውነታ ነው። ድርድሩ ውጤት እስኪያመጣ ድረስ ለመቀጠል መንግሥት ቁርጠኛ መሆኑን ወዳጅም ጠላትም ተረድቶታል። በዚያ አካባቢ ያለውን የሥጋት ሁኔታም ከቀረበለት ሪፖርት በመነሣት የደኅንነት ምክር ቤቱ የገመገመ ሲሆን፤ ሁኔታዎች ከጸጥታ አካላት ዐቅም በታች መሆናቸውንና በተገቢው መንገድ ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑን አረጋግጧል። ከግምገማው በመነሣት በአመራሩና በጸጥታ አካላት ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅጣጫዎችን አስቀምጧል።

በአጠቃላይ የውስጥ ተጋላጭነትን በመቀነስ፣ አገራዊ ደኅንነትን ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ አዎንታዊ ለውጥ መምጣቱን፣ የፀጥታና ደኅንነት ጉዳይ ለመንግስት ብቻ የሚሰጥ አለመሆኑን በመገንዘብ ሕዝቡም የሥራው ባለቤት እየሆነ መምጣቱን ከግምገማው ለመገንዘብ ተችሏል።

በሌላ በኩል ሥራዎች ገና አለመጠናቀቃቸውን፤ የጸጥታና ደኅንነት መዋቅሩ በሚጠበቀው መጠን አለመጥራቱን፤ የአመራሩንና የሕዝቡን የጸና ሥነ ልቡና የመገንባት ሥራ በተገቢው ልክ አለመሠራቱን፤ ጁንታው ከውስጥና ከውጭ ኃይሎች ጋር ሊያደርገው የሚፈልገውን ቅንጅት ለማምከን በልኩ አለመሠራቱን የደኅንነት ምክር ቤቱ ተመልክቷል።

እነዚህ ጉዳዮች በተገቢው ትኩረትና ቁርጠኝነት ካልተሠሩ የተገኘው አንጻራዊ ሰላም ዘላቂ እንደማይሆን ገምግሟል። በመሆኑም የሚከተሉት ተግባራት በአመራር፣ በጸጥታ አካላትና በሕዝቡ ቁርጠኝነትና መሥዋዕትነት ሊተገበሩ እንደሚገባ አቅጣጫ አስቀምጧል።

1. አሸባሪና ሕገ ወጥ ታጣቂዎችን ሥጋት ከማይሆኑበት ደረጃ ማድረስ፣

2. ሕዝብን በማወያየት፣ የታጠቁ አካላትን በማግባባት፣ ወጣቶችን በሰላም ተግባራት ላይ በማሳተፍ፣ ዘላቂ ሰላም የሚያረጋግጡ ሥራዎችን መሥራት፣

3. የፍትሕ አካላትን በማጥራትና በማጠናከር ለአገራዊ ሰላምና ደኅንነት የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ ማድረግ፣

4. ሕዝቡን በሚያማርሩ የኢኮኖሚ አሻጥር፣ የሙስና፣ የኮንትሮባንድ፣ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወዘተ ላይ የማያዳግም ርምጃ በመውሰድ ሕዝቡ እፎይ እንዲል ማድረግ፣

5. በየደረጃው ያለውን አመራር በማጥራትና ተጠያቂነትን በማስፈን፤ በየደረጃው ብቁ፣ ንቁና ወትሮ ዝግጁ የሆነ አመራር መፍጠር፣

6. ሕዝባዊና የሃይማኖት በዓላትን፣ የብሔርና የአስተዳደር እርከን ጥያቄዎችን፣ ጠላት የዓላማው ማስፈጸሚያና የሕዝቡን ሰላም ማወኪያ እንዳያደርጋቸው፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት መሥራት፣

7. በአፋርና በዒሳ መካከል፣ በአማራ ክልል የኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን የሚታዩ የጸጥታ ሥጋቶችን በዘላቂነት ለመፍታት ተገቢውን የፖለቲካና የጸጥታ ሥራ መሥራት፣

8. አልሸባብ ከውጭና ከውስጥ ኃይሎች ጋር ተቀናጅቶ የሥጋት መጠኑን ለመጨመር እንዳይችል፣ የተቀናጀ የጸጥታ ኃይሎችና የሕዝብ ሥምሪት ማካሄድና በቀጣናው ትርጉም ያለው ኃይል እንዳይሆን ማድረግ ቀጣይ ተግባሮቻችን ናቸው።

አመራሩ፣ የጸጥታ መዋቅሩና ሕዝቡ ተግባብቶና ተቀናጅቶ ሲሠራ ምን ዓይነት አመርቂ ውጤት እንደሚመዘገብ ካለፉት ሥራዎቻችን በሚገባ ተምረናል። በቀጣይም ይሄንኑ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል። እያንዳንዱን ተግባር ቆጥሮና ኃላፊነት ወስዶ ማከናወን፣ በየጊዜው መገምገም፣ የሠሩትን ማበረታታትና ኃላፊነታቸውን የማይወጡትንም መቅጣት ይገባል።

በእያንዳንዱ አካባቢ የሚከናወነው ጸጥታንና ደኅንነትን የማረጋገጥ ተግባር የመላዋ ኢትዮጵያ ሰላም የሚያጸና መሆኑን ማመን ያስፈልጋል። አጠቃላዩ ነገር የቅንጣቶቹ ድምር ውጤት፣ አንዳንዴም ከቅንጣቶቹ ድምር በላይ ነው። አጠቃላዩን የጸጥታና የደኅንነት ሁኔታ የተሻለ ለማድረግ እያንዳንዳችን በተሠማራንበት መስክ የምናከናውን ቅንጣት ተግባር በጥራትና በብቃት መወጣት ይገባናል።

ሕዝባችን ሰላሙና ደኅንነቱ ተረጋግጦለት ኢትዮጵያን ለማበልጸግ በሚደረገው ርብርብ ንቁ ተሳታፊ እንደሚሆን በየደረጃው በተካሄዱ ውይይቶች በአንድ ቃል ተናግሯል። በየጊዜው የምናደርጋቸው የግምገማ ውይይቶች፣ አዳዲስ ምክንያቶችን የምንሰማባቸው ሳይሆኑ፣ የችግሮችን መቀነስና የሰላምና ደኅንነትን መስፈን የሚያረጋግጡ መሆን አለባቸው። ይህ ደግሞ የሚሳካው ዕቅድን በሚገባ በመገንዘብ፣ የሚያስፈልገውን ሥምሪት በማካሄድና እስከ መጨረሻው ድረስ ለውጤቱ ብቻ በመድከም ነው።

ስለሆነም በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ የጸጥታ ኃይሉና ሕዝቡ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሆኖ የኢትዮጵያን ጸጥታና ደኅንነት ለማረጋገጥ እና ብልጽግናዋን እውን ለማድረግ ቁርጠኞች እንድንሆን ብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤቱ ጥሪ ያቀርባል።

**የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት**
**ነሐሴ 2፣ 2014 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ለዲጂታል ኢትዮጵያ እውንነት አንዱ አጋዥ መሳሪያ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

መንግስት አገሪቱ በሳይንስና ቴክኖሎጂው እንዲሁም በዲጂታል ኢኮኖሚው ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ እንድትችል፣ በእነዚህ ዘርፎች የሚከናወኑ ተግባሮችን በሚፈለገው ፍጥነትና የጥራት ደረጃ ለመስራት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች በመንደፍ ስራ ላይ አውሏል። ከእነዚህ ስትራቴጂዎች አንዱ “ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ» ነው።

የአገሪቱን ዲጂታል ኢኮኖሚ ጉዞ ለማሳለጥ እንዲሁም የኢትዮጵያን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን በግንባር ቀደምትነት ለመምራት የሚችሉና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ሊጠቀሙ የሚችሉ አራት ስትራቴጂያዊ ቅድሚያ የተሰጣቸው ዘርፎች መለየታቸውን በ “ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025” ስትራቴጂ ሰነድ ላይ ተመልክቷል። ለዚህም ግንባር ቀደም ተብለው ከተለዩት ውስጥ ግብርና፣ የማምረቻ ዘርፍ፣ የመረጃ ቴክኖሎጂና ቱሪዝም ዘርፎች መሆናቸው ተጠቁሟል።

ሁሉም ቁልፍ ዘርፎች ዘመኑ የሚጠይቀውን ሳይንሳዊና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንዲከተሉ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። አገሪቱ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ ወደኋላ ከቀሩት የዓለም አገሮች ጋር የምትመደብ መሆኗ እሙን ነው። ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ግን ተስፋ ሰጪ ጥረቶች እየታዩ ናቸው። ለእዚህም በግብርናው ዘርፍ ላይ በጎ ውጤት ሊያስከትል የሚችለውን የሳተላይት ቴክኖሎጂን፣ የቴሌኮም አገልግሎቶችን፣ የክፍያ ስርአቶችን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል።

ከዚህ አኳያ በቴሌኮም አገልግሎቶች በኩል በኢትዮ ቴሌኮም እየተከናወነ ያለውን ተግባር ሰሞኑን የቴሌ ብር የፋይናንስ አገልግሎቶች በተመረቁበት ወቅት የወጡ ዋና ዋና መረጃዎችን በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችን ይዘን ቀርበናል።

ኢትዮ ቴሌኮም ዘመኑ የደረሰበትን የቴሌኮም አገልግሎቶችን ማቅረቡን ቀጥሏል። በአፍሪካ ቀደምትና ለ128 ዓመታት የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የሆነው ኩባንያው፣ የቴሌኮም አገልግሎት ተደራሽነትን በከተማም በገጠርም ለማረጋገጥ ሲሰራ ቆይቷል። የኢትዮጵያውያንን ተጨማሪ እና ከፍተኛ አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ መድቦ የዘረጋውን መጠነ ሰፊ መሠረተ ልማት በመጠቀም “ቴሌብር” የተሰኘውን የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ባለፈው አመት መጀመሩ ይታወሳል።

የኩባንያው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ቴሌብር ወደ ስራ የገባው ግንቦት 3 ቀን 2013 ዓ.ም ነው። በዚህም የአገሪቱን የገንዘብ ዝውውር ስርዓት በማቀላጠፍና በማዘመን አስተማማኝና ምቹ የግብይት ስርዓት እንዲኖር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። አሰራሩ በርካታ ተቋማት ፈጣንና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ከደንበኞቻቸው ገንዘብ መሰብሰብ እንዲችሉና ደንበኞችም ካሉበት ሆነው ክፍያቸውን እንዲፈፅሙ አስችሏል።

አገልግሎቱ በጥሬ ገንዘብ ዝውውር ላይ ላሉ ውስንነቶች መፍትሄ ሆኖ ተገኝቷል። በቴሌ ብር አገልግሎት የግብር ክፍያ፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ድጋፍ፣ የአየር ሰዓት ሽያጭ እና የመሳሰሉትን መፈጸም ተችሏል። በዚህም እንግልትና ጥሬ ገንዘብ ይዞ መንቀሳቀስ ቀርቷል። በቅርቡ ተግባራዊ የተደረገውን የነዳጅ ድጎማ ክፍያም በቴሌ ብር እየተፈጸመ ይገኛል።

ቴሌ ብር ስራ ከጀመረ 14 ወራት ተቆጥረዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ብቻ 22 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የቴሌብር ደንበኞችን በቴሌ ብር ማፍራት ተችሏል። በዚህ ጊዜ የ34 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ግብይት/ ዝውውር ተፈፅሟል፤ አንድ ነጥብ 02 ሚሊዮን ዶላር ገንዘብ ከ37 አገራት ተልኮበታል፤ ይህ ውጤት ለሌሎች አገራትም በመልካም ተሞክሮነት የሚወሰድ እንደሆነም ተመስክሮለታል።

እስከ አሁን የአየር ሰአት ሲሞላበት፣ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የፋይናንስ ድጋፍና ሌሎች መሰል የዲጂታል ክፍያዎች ሲፈጸምበት፣ ህዝቡ ኑሮ እንዲቀል ሲደረግበት የቆየው ቴሌ ብር፣ እነሆ አሁን ደግሞ በቴሌ ብር ገና ብዙ እናያለን የሚያሰኙ አዳዲስ አገልግሎቶችን ይዞ ከተፍ ማለቱን ኢትዮ ቴሌኮም ሰሞኑን ይፋ አድርጓል።



ኢትዮ ቴሌኮም ከዳሸን ባንክ ጋር በመሆን ሰሞኑን የዲጂታል ፋይናንስ የቁጠባና ብድር አገልግሎቶችን በይፋ ባስጀመረበት ወቅት፤

ኢትዮ ቴሌኮም ከዳሸን ባንክ ጋር ይዟቸው የመጣውን እነዚህን አዳዲስ አገልግሎቶች ቴሌ ብር እንደ ኪሴ ወይም ኦቨር ድራፍት፣ ቴሌ ብር መላ ወይንም ክሬዲት ሰርቪስ እንዲሁም ቴሌ ብር ሳንዱቅ ወይም ሴቪንግ የሚሰኙ ናቸው። እነዚህን አገልግሎቶች ማግኘት የሚቻለውም በቴሌ ብር መተግበሪያ ወይም በቴሌብር አጭር ቁጥር ኮከብ 127 መሰላል ላይ በመጠቀም ይሆናል።

አገልግሎቱ ሰሞኑን በተጀመረበት ወቅት የብሄራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ፣ ከቴሌብር በፊት የኢትዮጵያ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ከአፍሪካ አገራት አንጻር እጅግ የወረደ እንደነበር አስታውሰዋል። አሁን የቴሌብርና ሌሎች የዲጂታል ፋይናንስ ተጠቃሚዎች ቁጥር በኢትዮጵያ ከ43 ሚሊዮን በላይ መድረሱን አስታውቀዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም ከዳሸን ባንክ ጋር በመተባበር ቴሌብር እንደ ኪሴ፣ ቴሌብር መላ (ብድር) እና ቴሌ ብር ሳንዱቅ (ቁጠባ) የተሰኙ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን ማስተዋወቁ ደግሞ የዲጂታል ኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት መጣሉን ያሳያል ብለዋል። ብሔራዊ ባንክ በቀጣይም ልክ እንደ ቴሌብር ሁሉ ከባንኮች ጋር በመተባበር የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት መስጠት ለሚፈልጉ ተቋማት ሁሉ አስፈላጊውን ፈቃድና አገዛ እንደሚያቀርብም አስታውቀዋል።

የዳሸን ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አስፋው አለሙ በበኩላቸው የአገልግሎቱን መጀመር የሐገራችን ልማት ዲጂታል እንቅስቃሴ አብነት ሲሉ ገልጸውታል። ዳሸን ባንክ የህልውና መሰረቱን ያጸናው የአገራችንን ጥቅምና የህብረተሰቡን እድገት ተቀዳሚ መርህ በማድረግ በተሰማራበት ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በሁሉም አቅጣጫ ምሳሌ የሚሆን ተግባር በማከናወን ጭምር ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ ባንኩ የኢትዮጵያ የባንክ ኢንዱስትሪን የሰለጠነው አለም በደረሰበት ዘመናዊ አገልግሎት ደረጃ ለማድረስና በቴክኖሎጂ የታገዙ አዳዲስ አሰራሮችን በመጀመር የፋና ወጊነት ሚናውን እየተጫወተ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

ባንኩ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ የዘለቀ አብሮ የመስራት የመተጋገዝ ግንኙነት እንዳለው አቶ አስፋው ጠቅሰው፣ ይህም ግንኙነት አድጎ ዛሬ የተሟላ የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳልሆኑ ለሚገመቱ 60 በመቶ ያህል ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እለታዊ የፋይናንስ ፍላጎታቸውን በማሟላት በየተሰማሩበት የስራ መስክ ራሳቸውን ለማሻሻል የሚችሉበትን የዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎት በአጋርነት ለመዘርጋት ያስችላል ሲሉ አብራርተዋል።

‹‹በዚህ አለም ስንኖር በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ማህበረሰቦችን ማገልገል፣ ችግራቸውን መፍታትን ያህል ምንም ነገር የለም›› ሲሉ የጠቀሱት የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ታምሩ፣ ‹‹ሰፊውን የማህበረሰብ ክፍል የፋይናንስ ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችለውን የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት መጀመር ስናበስር በታላቅ ደስታ ነው›› ብለዋል።

ዋና ስራ አስፈጻሚዋ እንዳሉት፤ የቴሌብር ፋይናንስ አገልግሎት ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ አጋዥ ከሆኑ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ነው። አገልግሎቱ ሰፊውን የማህበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ ያደርጋል። በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የኅብረተሰብ ክፍል ችግር ለማቃለል ይረዳል።

የፋይናንስ አገልግሎት ሲባል መቆጠብ ብቻ አይደለም፤ ማበደርንም ይጨምራል። የቴሌ ብር ፋይናንስ ኅብረተሰቡ የእለት ከዕለት እንቅስቃሴውን ለመምራትና ኑሮውን ለማሻሻል የሚረዳው አገልግሎት ነው። የተረጋጋ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት እንዲኖር ሰፊውን የማኅበረሰብ ክፍል የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለዚህም ነው አስፈላጊ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ተደርገው የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው።

ኩባንያው የአገሪቱን የዲጂታል ኢትዮጵያ ህልም እውን ለማድረግ በርካታ ተግባሮችን እያከናወነ መሆኑን ዋና ስራ አስፈጻሚዋ ጠቅሰው፣ ተደራሽነት ብቻ ሳይሆን አቅምን ያገናዘበ አገልግሎት ለመስጠት በርካታ ማሻሻያዎችን ሲሰራ መቆየቱንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረጉንም አስታውሰዋል።

ብድር ያለማስያዣ (Collateral) የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ ሰፊው የኅብረተሰብ ክፍል የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆን እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን ጠቅሰው፣ ይህን ችግር ለማቃለል ኢትዮ ቴሌኮም የቴሌብር ፋይናንስ አገልግሎት ፋይዳ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

ዋና ስራ አስፈጻሚዋ እንዳሉት፤ የቴሌ ብር የፋይናንስ አገልግሎት የእለት ተእለት ኑሮን በማሳለጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል፤ አሁን ደግሞ ገንዘብ ማስተላለፍ፣ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን መበደር ጭምር የሚያስችል አገልግሎት ኢትዮ ቴሌኮም ይዞ ቀርቧል።

ኢትዮ ቴሌኮም አገልግሎቱን በቴሌብር አማካኝነት ሲያቀርብ ዳሸን ባንክ ደግሞ የፋይናንስ አቅርቦቱን ያመቻቻል። ማንኛውም ደንበኛ ተያዥና ማስያዣ ንብረት ሳይጠየቅ የብድር አገልግሎት ማግኘት ይችላል።

ለቴሌብር የብድርና ቁጠባ አገልግሎት በዓመት 19 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ተዘጋጅቷል። የቴሌ ብር እንደ ኪሴ ደንበኞች በቴሌብር አካውንታቸው ላይ በቂ ገንዘብ ባይኖራቸው እንኳ፣ እስከ ሁለት ሺህ ብር ድረስ ተበድረው አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የሚያግዝ አገልግሎት ነው። በተጨማሪም ቴሌብር መላ ለደንበኞች ብድር የሚቀርብበት ሥርዓት ሲሆን፣ ቴሌብር ሳንዱቅ ደግሞ ቁጠባ አገልግሎት የሚሰጥበት ነው።

ለግለሰቦች እስከ 10 ሺህ ለአነስተኛ ተቋማት ደግሞ እስከ 100 ሺህ ብር የብድር አቅርቦት ተመቻችቷል፤ ይህም ለሥራ ዕድል ፈጠራና አብዛኛውን ኅብረተሰብ የፋይናንስ ተደራሽ ለማሳደግ የሚረዳ ቴክኖሎጂ ነው ።

ዋና ስራ አስፈጻሚዋ አገልግሎቶቹን አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ የመጀመሪያው ‹‹መላ›› የተሰኘ ሲሆን ግለሰብ ደንበኞች፣ ነጋዴዎች እንዲሁም ወኪሎች በቴሌብር ሂሳባቸው አማካኝነት አነስተኛ የብድር አገልግሎት (Micro Credit) የሚያገኙበት መንገድ ነው። ይህ አገልግሎት ሲቀርብ ብድር ያለማስያዣ ማግኘት ያስችላል፤ የደንበኞች መረጃዎች ምስጢራዊነትም ይጠበቃል። ሰዎች ራሳቸው ለራሳቸው ዋስ የሚሆኑበትን አሰራር የሚፈጥርና መተማመንን የሚያጎለብት ዘዴ ነው። ብድር በሚቀርብበት ጊዜ ደንበኛው በቴሌብር ላይ ያለው ተሳትፎ ይታያል።

ይህ የብድር አሰራር የፋይናንስ ውስንነት ያለባቸውን አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት በንግድ ስራ ላይ እንዲሰማሩና ስራውን ለማስፋት እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ልዩ ልዩ ተሰጥኦዎች ያሏቸው ወጣቶች በገንዘብ እጥረት ምክንያት ህልማቸው እንዳይጨናገፍ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙም ያስችላቸዋል። ቴሌብር መላ ለግለሰቦችና ለንግድ ተቋማት የቀን፣ የሳምንትና የወር አገልግሎቶች አሉት።

ሁለተኛው አገልግሎት ‹‹እንደ ኪሴ›› የተሰኘ ሲሆን የቴሌብር ደንበኞች በአካውንታቸው ላይ ያላቸው ቀሪ የሂሳብ መጠን በቂ ባልሆነበት ጊዜ የሚጠቀሙበት የብድር አገልግሎት (Micro Overdraft) ነው። ይህ አገልግሎት የጎደለውን የሚሞላ አጋር ነው። ቴሌብር ‹‹እንደ ኪሴ›› በቴሌ ብር ክፍያ የሚፈጸምባቸውን ሁሉንም አገልግሎቶችን የሚመለከት የቴሌብር ፋይናንስ ዘዴ ነው።

ሌላው የቴሌብር ፋይናንስ አገልግሎት ደንበኞች እንደየፍላጎታቸው ከወለድ ነፃ ወይም በየቀኑ የሚሰላ የወለድ መጠን የሚታሰብላቸው የቁጠባ አይነቶችን የሚጠቀሙበት ‹‹ሳንዱቅ›› የተሰኘው የቴሌብር አገልግሎት (Micro Saving) ሲሆን፤ አገልግሎቱ ትንንሽ ገንዘቦችን ለመቆጠብና ወደ ኢኮኖሚው ለማስገባት ያስችላል።

ይህ የቴሌብር ፋይናንስ አገልግሎት የክፍያ ስርዓቱን በማዘመን ሰፊው የኅብረተሰብ ክፍል የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ያግዛል። አገልግሎቱ አዳዲስ የሥራ እድሎችን በመፍጠር በአጠቃላይ አገራዊ ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱ ሚና ይኖረዋል።

በዚህ አገልግሎት የመጀመሪያው ዓመት ላይ 108 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ዝውውሮችን ለማከናወን ታቅዷል። በዓመቱ ለ12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ደንበኞች (Unique Users) ተደራሽ በመሆን በቴሌ ብር ‹‹መላ›› ዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ብድር ለመስጠት፣ በ‹‹እንደ ኪሴ›› ስድስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ለማበደር እንዲሁም በ‹‹ሳንዱቅ›› ደግሞ ሦስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ለመቆጠብ በአጠቃላይ የ19 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ብድርና ቁጠባ ለማከናወን ታቅዷል።

የፋይናንስ አገልግሎቱን ተደራሽነት ለማስፋት ብዙ ተሰርቷል፤ የቴሌ ብር የፋይናንስ ስርአትን ከስማርት ፎን በተጨማሪ በሌሎች የሞባይል ስልኮችም ይሰጣል። ለዚህም ተደራሽነት ሲባል ኮከብ 127 መሰላል መተገበሪያ ተዘጋጅቷል።

የፋይናንስ አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ አማራጮች መዘርጋታቸውም ተጠቁሟል። ኢትዮ ቴሌኮም ከ13 ባንኮች ጋር ትስስር ያለው በመሆኑ ደንበኞች ከአካውንቶቻቸው ገንዘብ ማንቀሳቀስ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ኩባንያው በየአካባቢው ከ79 ሺ በላይ ኤጀንቶች አዘጋጅቷል፤ በእነዚህ ኤጀንቶች በኩልም ገንዘብ ማስገባት ማውጣት የሚቻልበት ሁኔታ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም የኩባንያውን ምርቶች / ፕሮዳክትስ/ ለደንበኞች የሚያደርሱ ከ360 ሺ በላይ አጋሮች ያሉት በመሆኑም ለቴሌብር የፋይናንስ አገልግሎት ሌሎች አማራጮች ተደርገው ያገለግላሉ።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የማክሮ ኢኮኖሚ ስኬት

**ምህረት ሞገስ**

ማክሮ ኢኮኖሚ የአገር ውስጥ ምርት፣ አገራዊ ገቢ፣ የሥራ ዕድል እና ሥራ አጥነትን እንዲሁም የኑሮ ውድነትን እንደሚያካትት የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። በኢትዮጵያም የብሔራዊ ማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ ባደረገው ግምገማ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ2014 በጀት ዓመት በተለያዩ መመዘኛዎች ስኬት ማስመዝገቡ መግባባት ላይ ተደርሷል።

ግምገማው በተካሔደበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደገለጹት፣ በወጪ ንግድ ዘንድሮ ከ10 ነጥብ 2 እና 3 ቢሊዮን ዶላር በላይ ከአገልግሎት ዘርፍ ብቻ ማግኘት ተችሏል። ይህ የሆነው ከዳያስፖራ የሚላከው እና የወጪ ቀጥተኛ ንግድ ኢንቨስትመንት ሳይጨመር ነው። ሁለቱ ሲጨመሩ ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር ይደርሳል። ይህ ለኢትዮጵያ ትልቅ አይደለም። ኢትዮጵያ ከዚህም በላይ ከዚህ አምስት እና ስድስት ሰባት እጥፍ ማግኘት እና ማደግ ትችላለች፤ ነገር ግን ኢትዮጵያ ከነበረችበት ሁኔታ አንፃር ይህ በጣም ትልቅ እምርታ ነው።

ይህ ውጤት አንድም በበጀት ዓመቱ ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ በመቻሉ እና የግብርናው ዘርፍ ዕድገት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማስመዝገብ ረገድ ከፍተኛ ውጤት በማምጣቱ መሆኑን የሚገልጹት ደግሞ የግብርና ሚኒስቴር ዑመር ሁሴን ናቸው።

እንደሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ በአራት ነገር ላይ ትኩረት በማድረግ የወጪ ምርትን ብቻ ሳይሆን ወደ አገር የሚገባ ምርትን የመተካት ሥራ ተሠርቷል ። በዚህ ውስጥ የአርሶ አደሩን ገቢ ማሳደግ እና የሥራ ዕድል መፍጠርም ሌላኛው ትኩረት ሆኖ ሲሠራበት ከርሟል። በተለይ የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ገቢ አብዛኛው ከቡና ምርት በመሆኑ ቡናን በጥራት ለዓለም ገበያ ለማቅረብ በተሠራው ሥራ ከዚህ ቀደም ሲነሱ የነበሩ ችግሮችን መፍታት ተችሏል።

ሁልጊዜ ለዓመታት የተተከለው የቡና እግር ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ከአረንጓዴ ልማቱ ጎን ለጎን በተለያዩ ክልሎች ከሶስት ሚሊዮን ችግኝ በላይ ተተክሏል። ይህም ከአራት ዓመት በኋላ በአስተማማኝ መልኩ እንዲቀጥል በሚያስችል መልኩ እየተሠራ መሆኑን ያመለክታል።

ሌላው ማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ስኬት እንዲገኝ በማስቻል በኩል ተጠቃሹ የትራንስፖርት ዘርፍ ነው። የአገሪቱን የወጪ እና የገቢ ንግድ በማሳለጥ ለተጠቃሚው እንዲደርስ በማድረግ ረገድ የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክ ሚኒስቴር ከፍተኛ ውጤት የተመዘገበባቸውን ሥራዎች ሰርተዋል የሚሉት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክ ሚኒስትሯ ዳግማዊት ሞገስ ናቸው።

እንደሚኒስትሯ ማብራሪያ፤ የማዳበሪያ አቅርቦትን በጊዜው በማድረስ የተገኘውን ስኬት በማሳያነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። ከወጪ እና ከገቢ ንግድ ጋር ተያይዞ የተመሰረቱ ምርቶችን ለዓለም ገበያ ለማቅረብ፤ ከውጭም የሚገቡትን ምርቶችን ወደ አገር አምጥቶ እስከ መጨረሻው ተጠቃሚ ከማድረስ አንፃር የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክ ሚናውን በአግባቡ ተወጥቷል።

በዚህ ዓመት ከ 13 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን በላይ ወደ አገር የሚገባ ምርት ነበር። ከዚህ ውስጥ የማዳበሪያ ግብዓትን ማንሳት ይቻላል። ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ ላይ ብቻ ጥገኛ በመሆኗ በወጪ እና ገቢ ንግድ ዘርፍ በርካታ ችግሮች እንደነበሩ የሚታወስ ቢሆንም፤ ተጨማሪ ወደቦችን መጠቀም በመቻሉ የመርከቦችን የቆይታ ጊዜ እና የውጭ ምንዛሪ ወጪን መቀነስ ተችሏል። የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 98 እና 99 በመቶ ይደርስ የነበረ ቢሆንም፤ በእዚህ ዓመት ግን ወደ 84 በመቶ ማውረድ ተችሏል። ይህ የሆነው የታጁራ ወደብን የመጠቀም ድርሻ ከዘጠኝ በመቶ በላይ ከፍ ማድረግ በመቻሉ እና የበርበራ ወደብንም እንደዚሁ መጠቀም በመቻሉ መሆኑን አመላክተዋል።

ሌላው ኢትዮጵያ በማክሮ ኢኮኖሚ የተሻለ አፈፃፀም እንዲታይባት ካስቻሉት መካከል የባንኩ ዘርፍ ሌላኛው ነው። ባንኩን በተመለከተ በተቀማጭ የሀብት መጠን ብድር በማስመለስ ምጣኔ እና በሌሎች የጤናማነት መለኪያዎች የተሻለ አፈፃፀም ማስመዝገብ መቻሉ



የወጪ ንግድ ላይ መናር ያለበት ዕይታ ልክ እንደወተቱ ነው

**መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል ከቀረጥ ነፃ በማስገባት ማግኘት ከሚገባው ገቢ እስከ 50 ቢሊዮን ብር ነው ያጣው፤ ችግሩን ለማቃለል ከሚፈለገው በላይ ገንዘብ ወደ ገበያ እንዳይገባ መቆጣጠር እና ድህነትን የሚቀንሱ የልማት ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት፤ በአገር ውስጥ ያለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ያስችላል**

ታውቋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ ዶክተር ይናገር ደሴ እንደሚናገሩት፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የባንኮች ተቀማጭ ሀብት አንድ ነጥብ ሰባት ትሪሊዮን ብር ደርሷል። ይሄ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር 26 ነጥብ 7 በመቶ አድጓል። ባለፈው አንድ ዓመት ባንኮች ብድር የማስመለስ አቅማቸውን በ48 ነጥብ 7 በመቶ ማሳደግ ችለዋል። ለግሉ ዘርፍ የሚያቀርቡት የብድር ምጣኔም በከፍተኛ መጠን የጨመረ ሲሆን ይህም በአጠቃላይ የባንኩ ዘርፍ በተሻለ አፈፃፀም ላይ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

በዓለምም ሆነ በአገር ደረጃ አንዳንድ ነገሮች ቢያጋጥሙም የፋይናንስ ዘርፉ ጤናማ ዕድገት አሳይቷል። በ2014 በጀት ዓመት የፋይናንስ ዘርፉ አፈፃፀሙ በጥሩ ሁኔታ አልቋል። ለግል ዘርፉ የሚቀርበው የውጭ ምንዛሬ መጠንም በከፍተኛ መጠን ጨምሯል። በሌላ በኩል የቴሌ ብር ወደ ሥራ መግባቱን ተከትሎ ዲጂታል ፋይናንስ ሥርዓት እየጎለበተ መጥቷል። ይህም ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውርን እና ኮንትሮባንድን በመቆጣጠር የዋጋ ግሽበት እንዲረጋጋ እንደሚያግዝም ተናግረዋል። ይህ ሁሉ ቢሆንም ለግል ዘርፉ የሚቀርበው የውጭ ምንዛሬ መጠን በቂ አለመሆኑ አሁንም በድክመት የሚነሳ ነው።

የንግዱ ማሕበረሰብ እና አጠቃላይ የግል ዘርፉ የውጭ ምንዛሪን በሚፈልገው መጠን ማግኘት ባለመቻሉ የውጭ ምንዛሪ ተመኑ በባንኮች እና በውጭ በሚመነዘረው መካከል በየጊዜው እየሰፋ መሆኑ ታይቷል። ይህንን ለመቀነስ የውጭ ምንዛሪ ማግኛ መንገዶች ላይ በስፋት መሠራት እንዳለበት ጠቁመዋል።

የብሔራዊ ማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ አባል አቶ ተክለወልድ አጥናፉ በበኩላቸው፤ የፋይናንስ ዘርፉን ለማሻሻል የተከናወኑ የለውጥ ሥራዎች ዘርፉን ከውድቀት እንደታደጉት በመጠቆም፤ ለአብነት ባለፉት 4 ዓመታት የባንኮች ቅርንጫፍ ቁጥር በ30 በመቶ ማደጉን ይገልጻሉ። በዚህ ምክንያት ቅርንጫፎቹ 8 ሺህ ደርሰዋል። 82 ሚሊዮን ዜጎች የቁጠባ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መሰራቱንም አብራርተዋል። ነገር ግን ከዓለም አቀፉ ጂኦ ፖለቲካ መለወጥ ጋር ተያይዞ የዋጋ ንረት አሁንም የኢትዮጵያ ፈተና ሆኖ መቀጠሉን በማስታወስ፤ ተጎጂዎችን ለመታደግ ግብርና መስኖ እንዲሁም ለመንገድ በአጠቃላይ የመንግሥትን በጀት 59 በመቶ የሚሆነውን ወጪ በማውጣት ሕብረተሰቡ የኑሮ ሁኔታው እንዲረጋጋ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል ከቀረጥ ነፃ በማስገባት ማግኘት ከሚገባው ገቢ እስከ 50 ቢሊዮን ብር ነው ያጣው፤ ችግሩን ለማቃለል ከሚፈለገው በላይ ገንዘብ ወደ ገበያ እንዳይገባ መቆጣጠር እና ድህነትን የሚቀንሱ የልማት ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት፤ በአገር ውስጥ ያለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ያስችላል።

በቀጣይ የወጪ ንግድ ላይ ምን ያህል ትኩረት መሠጠት እንዳበት እና የወጪ ንግድም ዋነኛው መሠረት መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በምሳሌ አስደግፈው ሲያብራሩ «የወጪ ንግድ መታየት ያለበት እንደወተት ነው። ወተት በዕለቱ ይጠጣል፤ ይሸጣል። ሲያድር ይረጋል፤ እርጎውም ይሸጣል፤ ይጠጣል። በመቆየቱ ዋጋው አይቀንስም። እርጎ መሸጥ ያልፈለገ ሰው አይብ አድርጎ ይሸጠዋል። ወይም ቂቤ ያወጣል። አሬራው ሳይቀር ይጠጣል። የወጪ ንግድ እንደዚህ ነው። ዛሬ አራት ሚሊዮን ዶላር ቢመጣ ዕዳ እና የፍጆታ ፍላጎትን መሸፈን ይቻላል። ከፊሉን ተጠቅመን ከፊሉን እናቆየው እና መጠባበቂያ ይሁን ካተባለም በማንኛውም ሰዓት የሚመነዘር በመሆኑ ማቆየት ይቻላል።» በማለት ለማክሮ ኢኮኖሚ የወጪ ንግድ ዘርፉ ምን ያህል የደም ስር እንደሆነ ያስረዳሉ። የተከማቸ ዕዳ ለመቀነስ እና አዳዲስ ፕሮጀክት ለመጀመር እና የገበያ መረጋጋት ለመፍጠር ለሁሉም የወጪ ንግድ አስፈላጊ ነው ይላሉ።

የወጪ ንግድ ላይ ያልተሳካለት ኢኮኖሚ በብዙ ምክንያት ማደግ አይችልም። ምንም እንኳ የማክሮ አመላካቾች ብዙ ቢሆኑም ዋናው ግን በወጪ ንግድ ምን አመጣሁ? የሚለው ነው። እርሱ ሲስተካከል ብዙዎቹን አመላካቾችን መቀየር ማደግ እና ማስተካከል ይቻላል ብለዋል።

እንደጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ ለምሳሌ በውጭ ምንዛሪ ግብርና ማደግ ይችላል። አርሶ አደሩ ማሽኖችን ካስገባን እና መስኖ እንዲሠራ ካገዝነው «ምርቴን አሳድጋለሁ» ይላል። ስለዚህ የወጪ ንግድ ካደገ እና ገንዘብ ካለ ግብርናን መደገፍ ይቻላል። አርሶ አደሩ የሎጀስቲክ ጥያቄ ካቀረበ እና መንገድ ካልሠራችሁልኝ መኪና ካላመጣችሁልኝ እንዴት ችግሬን እፈታለሁ? ካለ ምላሽ መስጠት የሚቻለው የውጭ ምንዛሪ ካለ ብቻ ነው። ስለዚህ በወጪ ንግድ ላይ እድገት መጣ ማለት ሌሎቹን ዘርፎች እየደገፈ የሚፈለገውን ውጤት መምጣት ይቻላል። የወጪ ንግድ ላይ ሳይሳካ የግብርና ምርት ቢያድግም 20 እጥፍም ቢሆን በውስጥ ችግር ባይኖርም አስተማማኝ ማድረግ አይቻልም።

የወጪ ንግድ ላይ መናር ያለበት ዕይታ ልክ እንደወተቱ ነው። በማንኛውም ጊዜ የማይወድቅ የሚበላ የሚሸጥ የሚጠቅም መሆኑ መዘንጋት የለበትም። የተሻለ እምርታ የመጡት የወጪ ንግድን ያሳደጉ አገራት ብቻ ናቸው ፤ ይህ መሆኑ በደንብ መያዝ እና በዚህ ሃሳብ ላይ መሰራት አለበት። ይህ ሲባል የግብርና ምርትን ወደ ውጪ በመላክ ብቻ ሳይሆን እንደቱሪዝም ያሉ ሌሎች ዘርፎች ላይም ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንዳለበት ያብራራሉ።

ከቱሪዝም አንፃር እንደ ኢትዮጵያ ሊሸጥ የሚችል ሀብት ያለው አገር እንደሌለ በመጥቀስ፤ ታሪክ፣ ታይተው የማይጠገቡ ሰንሰለታማ ተራሮች እንዲሁም የዱር አራዊት እና ሌሎችም የአገሪቷ መልከዓ ምድር ያቀፋቸው ሀብቶች ቢኖሩም የአገልግሎት ኢንዱስትሪው ዘምኖ መሸጥ ካልቻለ መጠቀም እንደማይቻል ያስረዳሉ።

በቱሪዝም ሌሎች አገራት ፀሃይ፣ አሸዋ እና ባህር ብቻ ይዘው አሸዋ ላይ ዛፍ በመትከል ውሃውን ገፍተው አስደማሚ ሪዞርት በመገንባት ብዙ እያገኙ መሆኑን በማስታወስ፤ ባህርዳር እና ጎርጎራ መሃከል ላይ ያለውን ደጋ እስጢፋኖስን በማስጎብኘት ዛሬም ድረስ አፅማቸው ሳይበሰብስ የቆዩትን ነገሥታት እና በዚያ ዘመን ከ500 ዓመት በፊት በምን ዓይነት ዕቃ የነገሥታቱን አፅም ማቆየት እንደተቻለ ማሳየት ቢቻል ትልልቅ ውጤቶችን ማግኘት ይቻላል ይላሉ።

የህዳሴው ግድብ አካባቢም ብዙ የከፍታ ቦታዎች በመኖራቸው፤ አንድ ከፍታ ለአንድ ሪዞርት በማለት ብዙ መጠቀም እንደሚቻል እና እንደውም የቆየ ውሃ እና ባህር ሳይሆን ትኩስ ውሃ ላይ መዝናኛን በመፍጠር ብዙ መጠቀም እንደሚቻል ለዚህም ብዙ አቅም መኖሩን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስረድተዋል።

ከሁሉ በላይ ግን የሰው ሃይልን መጠቀም ነው ካሉ በኋላ፤ ብዙ አገራት መቀጠል የቻሉት በቂ የሰው ሃይል ስለነበራቸው መሆኑን ገልፀዋል። ነገር ግን ቁጥራቸው አነስተኛ ሆኖ በጣም በርካታ ሰውን ከውጪ ያመጡ አገራት የውጪው ሰው ጥሎ ሲሔድ ወደቡም ሆቴሉም ዝግ እንደሚሆን በማስታወስ፤ አገሬ ብሎ ሞትን የሚጋፈጥ ሰውን በማሰማራት፣ በማስተማር እና በማቅናት ሕዝቡን ሥራ ወዳድ ማድረግ ከተቻለ ትልቅ ለውጥ የሚመጣ መሆኑን ገልፀዋል።

በተቃራኒው በከፍተኛ ደረጃ እርዳታ የሚጠብቅ እና የልመና ባህልን የተለማመደ ትውልድ እየተፈጠረ ከቀጠለ ለብልፅግና ፀር መሆኑን ጠቁመዋል። ቁጭ ብሎ በሰበብ አስባቡ ችግር ተናግሮ መረዳት የሚያስብ ሃይል ሳይሆን ሰርቶ ደክሞ ለውጥ የሚያመጣ ሃይል መፈጠር ከተቻለ የማክሮ ኢኮኖሚው ስኬት ከዚህም በላይ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል። ሃይል እና ማዕድን ኢንዱስትሪን በጣም ስለሚያግዙ ሁለቱ ላይ ለየት ያለ ሥራ በቀጣይ መስራት እንደሚኖርበትም አክለዋል።

ሚኒስትሯ ዳግማዊት ሞገስ በበኩላቸው በ2014 በጀት ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የሞያሌ ኮሊደርን የሞምባሳ ወደብን በመጠቀም ምርቶችን ወደ ሀገር ቤት ማስገባት የተቻለ ቢሆንም፤ በ2015 በጀት ዓመት ከዚህ የላቀ ስኬት ለማስመዝገብ እንደሚሠሩ እና ትልቅ ውጤት ይገኛል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሃሳብ በሚደግፍ መልኩ የተናገሩት ዶክተር ይናገር ደሴም በቀጣይ የወጪ ንግድን ጨምሮ የውጭ ምንዛሬን ግኝቱን የሚያሻሽሉ ተግባራትን በማከናወን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ ይሠራል የሚል እምነት እንዳላቸው በመጠቆም፤ በ2015 በጀት ዓመት በወጪ ንግድ ላይ ከፍተኛ ርብርብ ለማድረግ የተለጠጠ ዕቅድ መታቀዱን እና በግብርናና በማኑፋክቸሪንግ እንዲሁም በማዕድን እና በቱሪዝም ላይ ትልልቅ ሥራዎችን በመሥራት የውጭ ምንዛሪ ሊገኝባቸው የሚችሉ አማራጮች በማስፋት ከዚህ የተሻለ ውጤት ለማምጣት መታቀዱን አመላክተዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## አጭር ቀሚስ ከሴቶች መብት መከበር፤ ከስርአተ ጾታ ፍትሃዊነትና እኩልነት አኳያ

**ሰላማዊት ውቤ**

በኢትዮጵያ አለባበስን የሚደነግግ ሕግ የለም። ሆኖም በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅና በወንጀል ሕግ በሥራ ቦታቸው ላይ ጉንተላንም ሆነ ሌሎች ጾታዊና ወሲባዊ ጥቃቶችን በሴቶች ላይ የሚፈፅሙ ክፍሎችን የሚቀጣ ሕግ አለ። ሕጉ ሴት አስተናጋጆች ከቀጣሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። በሕገ-መንግስቱም እንዲሁ ስለሴቶች መብትና ጥቃት ተቀምጧል። አሁን በመዲናችን አንዳንድ አካባቢዎች እንደሚስተዋለው ሴት አስተናጋጆች ከተቀጠሩበት ዓላማ ውጪ መጠጥና ምግብ ለማሻሻጫ እንዲውሉ እየተደረጉ ነው ከመባሉ ጋር ተያይዞ አንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶችና ህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አስፈላጊ ከሆነም በጥናት ላይ ተመስርቶ ሕግ ማውጣት ይችላል ሲሉ ምላሽ የሰጡን በመዲናችን አዲስ አበባ ብሎም በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች በሚገኙ ሥጋ ቤቶችና ምግብ ቤቶች የሚያስተናግዱ ሴቶች በአሰሪዎቻቸውና በአስቀጣሪዎቻቸው አጭር ቀሚስ እንዲለብሱ የመገደዳቸው አጀንዳ መነጋገርያ መሆኑን አስመልክተን ስለ ሕግ መሰረቱና መፍትሄዎቹ ዙርያ ያነጋገርናቸው ወይዘሮ ሜሮን አራጋው ናቸው።

ወይዘሮ ሜሮን የአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ምክትል ኃላፊና የሴቶች ዘርፍ ኃላፊ ሲሆኑ፤ እንደወጣትነታቸው (ወጣቷን ኃላፊ) በአለባበስ ዙርያ የግል አስተያየታቸውንም ጠይቀናቸው አጋርተውናል። ጽሑፋችንን ከዚሁ እንጀምራለን።

ኃላፊዋ የግል አለባበሳቸውን በተመለከተ እንደማንኛዋም ወጣት ሴት የራሳቸው ምርጫ እንዳላቸው ነግረውናል። በአደኩበት፤ አስተዳደግ፤ በማምነው ዕምነትና በበባህሌ ስነ ምግባር የተሞላባቸው የምላቸው አለባበሶችን እከተላለሁ። ይሄ የኔ ትርጉም አሰጣጥ ለሌላኛው ትክክል ነው ማለት አይደለም ይላልም ወይዘሮ ሜሮን። እንደሳቸው ሁሉ ሌሎች ከወጣትነት በላይም ሆኑ ከወጣትነት በታች ያሉ ሴቶች የየራሳቸው ምርጫ አላቸው። በመሆኑም አለባበስ የምርጫ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላሉ።

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህሎች፤ የበርካታ ሐይማኖቶችና እሴቶች ባለቤት ነች። እንደየ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የአለባበስ ምርጫዎቻችን የተለያዩ ናቸውም ይላሉ ኃላፊዋ። የአለባበስ ምርጫ እንደየአስተዳደጋችን፤ እንደ ባህላችን፤ እንደ ምንኖርበት ሁኔታ ይወሰናልም ባይ ናቸው። ከዚህ ባሻገርም በአለባበሳችን ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችም አሉ። ዓለም አቀፍ ፋሽኖችን መከተል፤ ዘመን አመጣሽ ልብሶችን መልበስ የየአንዳንዱ ግለሰብ ምርጫ እና መብት ነው።

ኃላፊዋ የአጭሩ ቀሚስ አጀንዳ በዋናነት ከሴቶች መብት መከበር፤ ከስርዓተ ጾታ ፍትሃዊነት፣ እንዲሁም እኩልነት ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው ይላሉ።

አለባበስ የግለሰብ የምርጫ ጉዳይና መብት ነው የሚሉት ወጣቷ የስራ ኃላፊ አስተናጋጅ ሴቶች በሥራ ቦታቸው ላይ አጭር ቀሚስ እንዲለብሱ በአሰሪዎቻቸው የመገደዳቸውን ቅሬታ በተለያየ መንገድ ማንሳታቸውንም ያወሳሉ። በዋናነት የአብዛኞቹ አስተናጋጅ ሴቶች ቅሬታ አጭር ቀሚስ በመልበሳችን ውርጩና ብርዱ እጅግ በከበደበት የዘንድሮ ክረምት ለተለያየ የጤና እክል እየተጋለጥን ነው የሚል እንደሆነም ይጠቅሳሉ። የጤንነታቸው ጉዳይ በሕክምና ከተረጋገጠና አሰሪያቸው አጭሩን ቀሚስ እንዲለብሱ የሚያስገድዳቸው ከሆነ በሕግ የሚያስጠይቀው እንደሆነም ይናገራሉ። አንዳንዶቹ አስተናጋጆች "አጭሩን ቀሚስ አለብስም" በማለታቸው ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይባረራሉ። እስከ መደብደብም የሚደርሱ አሉ። ይህን የምናገረው ዝም ብዬ አይደለም፤ ሴት አስተናጋጆቹ በተለያየ ጊዜ



ወይዘሮ ሜሮን አርጋው

የገለፁትን እንዲሁም ከሴቶች ጋር በተያያዘ የሚሰሩ ተቋማት የሰሩትን ዳሰሳ መሰረት አድርጌም ነው ይላሉ። እንደሳቸው ይሄ ተግባር ሕገወጥ ድርጊት ነው። አሰሪና ሰራተኛ ተስማምቶ የሚኖርበት ስምምነት አለ። ከዛ ስምምነት ውጪ ሰብዓዊ መብትንና ሰብአዊ ክብርን የሚነካ ጉዳይ ወንድም ሆነ ሴት ላይ ከተፈፀመ የሚቀጣ ሕግ አለን ይላሉ። ለአብነትም ስለዚህ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/11ን ይገልፃሉ። በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ላይ በግልጽ መስፈሩንም ያነሳሉ። እንደሳቸው ማብራሪያ ሴት አስተናጋጆች ከቀጣሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ነው። በመሆኑም በሥራ ግንኙነታቸው ላይ በሚያጋጥማቸው እክል አሰሪዎቻቸውን መጠየቅ ይችላሉ። ከወንዶች ባልደረቦቻቸው ጋር እኩል ሥራ እየሰሩ እኩል ክፍያ የማይከፈላቸው ከሆነ እንዲሁም በሥራ ቦታቸው ላይ ጉንተላ፤ ወሲባዊ ትንኮሳና ሌሎች ጥቃቶች የሚደርስባቸው ከሆነ ሕጎች አሉ። አለባበሳቸውን ተከትሎ ለሚደርስባቸው አስገድዶ መድፈርም ሆነ ሌላ ጾታዊ ጥቃት የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አንቀጽ 4 ላይ በግልጽ መቀመጡንም ይጠቅሳሉ።

አጠቃላይ ጾታዊ ጥቃት ሥራ ከተቀጠሩ በኋላ ጤናችን ላይ ችግር ስለሚያጋጥመን ይሄን ቀሚስ አንለብስም ስለዚህ ቀሚሱን በሱሪ እንቀይረው ወይም በሚመቸንና የጤና ሁኔታችን በሚፈቅደው እናድርገው ሲሉ አይ ጤናሽ እየተበደለም ቢሆን ቀሚሱን ለብሰሽ ስራሽን መሥራት አለብሽ የሚል አሰሪ ካለ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል። ይሄ የወንጀል ሕጉና ሕገ መንግስቱም ላይ ሰፍሯል። ሕገ መንግስቱ ላይ ሴቶች ከወንዶች እኩል መብቶቻቸውን ኤክሰርሳይ (ተግባራዊ) ማድረግ አለባቸው ይላል። ከዚሁ ጋር ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ ማግኘት፤ ቅጥር ላይ፤ ዕድገት ላይ በተፈጥሮ ካላቸው ልዩነት ውጪ ከወንዶች እኩል ክብካቤ የማግኘትና የመጠቀም መብት እንዳላቸው ተደንግጓል።

እርግጥ ነው፣ አንዳንዴ እንደቢሮ ስናየው እንዲህ ዓይነት ህጎችን በማስፈፀም ሂደት ላይ ክፍተቶች ይገጥማሉ። ለአብነት አንዲት አስገድዶ መድፈር የደረሰባትን ሴት አስመልክቶ ያለውን ክፍተት ማሳያ ያደርጋሉ። እንደ ተቋም ባይሆንም በተቋም ውስጥ እንዳሉ ባለሙያዎች ሕብረተሰቡ ውስጥ ለሴቷ የሚሰጠው ቦታም በባለሙያዎች የሚንፀባረቅበትና ቢሯቸው ከሥር ከሥር እያረመ የሚሄድበት ጊዜ ብዙ ነው። ለአብነት እንዳነሱት አንዲት ሴት አስገድዶ መደፈር ደርሶባት ወደ ፍትህ አካላት በምትሄድበት ጊዜ ቀድሞ የሚነሳው ምን ለብሳ ነበር የሚለው ጥያቄ ነው። ለምን አመሸሽና ለምንስ ብቻሽን ሄድሽም የሚል ተበዳይዋን የሚያሸማቅቅ ጥያቄም አለ። አጭር ቀሚስ ለብሳ የነበረ በመሆኑ አነሳስታው ነው የደፈራት ያለም ባለሙያ ገጥሟቸው ያውቃል።

አስተናጋጆቹ አጭር ቀሚስ በመልበሳቸው ሙሉ በሚባል ደረጃ አካላቸው ግልጽ ነው የሚሉት ኃላፊዋ ኢትዮጵያ የተለያዩ ዕምነቶችና ባህሎች ያሉባት አገር መሆኗንም ያወሳሉ። ከዚህ አንፃር ሕብረተሰቡ አጭር መልበሳቸውን ላይፈልገው ይችላል። በዚህ የተነሳም ሊያገላቸው፤ ለባሾቹ ራሳቸውም ሞራላቸው የማይፈልገው ሁኔታ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። አለባበሳቸውን ተከትሎ የሚደርስባቸው ወሲባዊ ትንኮሳ፤ ወሲባዊ ጥያቄ ሊቀርብላቸው፤ በአጠቃላይም ከተቀጠሩበት ዓላማ ውጪ የሆኑ ጉዳዮችን እንዲያስተናግዱና እንዲሸማቀቁ ይዳረጋሉ። ተገልጋዮቹ አገልግሎት የሚሰጥበት መዝናኛ ወይም ምግብና መጠጥ ቤት የሚመጡት አገልግሎቱን አግኝተው ለመሄድ ብቻ ላይሆን ይችላል። ከዚህ አንፃር አሰሪዎቻቸውም የያዙት ሴቶቹን እንደ ማሻሻጫ ማቅረብም ጭምር ነው። ሆኖም ሴት አስተናጋጆች ለምግብና መጠጥ ማሻሻጫ መልበስ (መዋል) የለባቸውም። ሴቶቹ በሚያስተናግዱበት ወቅት ሥራ ላይ የሚደርስባቸው ማንኛውም ተፅዕኖና የመብት ጥሰት አልፎ ተርፎም ሥራ ላይ በሚደርባቸው ጾታዊ ጥቃት የሕግ ከለላ አላቸውም ባይ ናቸው። በሥራ ገበታቸው ላይ ይሄንኑ መብታቸውን ከግንዛቤ እንዲያስገቡም ይመክራሉ።

ሆኖም አስተናጋጅ የሆኑ ሴቶች በሥራ ቦታዎቻቸው ላይ እንዲለብሱ የሚገደዱት አጫጭር ቀሚሶችን በተመለከተ ምን ህግ አለ፤ ወደ የሚለው ሲመጣ በኢትዮጵያ አለባበስን የሚደነግግ ሕግ የለም ይላሉ ኃላፊዋ። በመሆኑም እከሌ ይሄን ልብስ በመልበሷ ትክክል ነች፤ ወይም ትክክል አይደለችም ብሎ መፈረጅ አስቸጋሪ እንደሆነም ያወሳሉ።

ነገር ግን አሁን በተጨባጭ በምግብና መጠጥ ቤቶች፤ መዝናኛ ቦታዎች በሴት አስተናጋጆች ላይ የሚደርሰውን አጭር ቀሚስ ካለበሽ አታስተናግጂም፤ ከሥራ ትባረሪያለሽ የሚል በደልና ጥቃት አስመልክቶ በጥናት ላይ ተደግፎ ሕግ ማውጣት አስፈላጊም እንደሆነ ይጠቅሳሉ ኃላፊዋ። አስተናጋጆችን አጭር ቀሚስ ልበሱ ብሎ ማስገደዱ ሴቶች ላይ፣ እኩል ተሳትፏቸው ላይ፣ ጤና ጉዳያቸው ላይ እና መብቶቻቸውን ከማስከበር አንፃር ችግር ይፈጥራል ከተባለ እንደ ከተማ አስተዳደር ጥናት ተሰርቶ በጥናቱ መሰረት ሴቶች በአሰሪዎቻቸው ተገድደው በሥራ ቦታቸው ላይ አጭር ቀሚሱን ለብሰው መሥራት የለባቸውም የሚል ሕግ ማውጣት እንደሚቻልም ያስረዳሉ።

‹‹በጥናት ላይ ተመስርቶ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ነው›› የሚሉት ወይዘሮ ሜሮን በጥናት ላይ የተደገፈ ሕግ በሌለበት ሁኔታ አሰሪዎቻቸውን ወይም ራሳቸውን አስተናጋጆቹን ጭምር ይሄን ልብስ ለምን ለበሳችሁና ልበሱ አላችሁ ብሎ መጠየቅ እንደማይቻልም ያስገነዝባሉ። ነገር ግን አንዲት አስተናጋጅ አሰሪዋን በዕወቀቷ፣ በጉልበቷ የማስተናገድ፤ ቀጣሪው ድርጅት ደግሞ በአግባቡ እስካገለገለች ድረስ በውሉ መሰረት ክፍያዋን የመፈፀም ግዴታዎች አሉባቸው። ሴት አስተናጋጆች ከዚህ አልፈው መብተን የሚነኩ ጉንተላዎችን፤ ጾታዊና ወሲባዊ ጥቃቶችንና ትንኮሳዎች ሲደርሱባቸው በአገራችን ወንጀል ህግ ስነስርዓት መጠየቅና መብቶቻቸውን ማስከበር ይችላሉም ብለዋል ወይዘሮ ሜሮን።

በተጨማሪም፣ አስተናጋጆችም ሆኑ ሌሎች ሴቶች ተገድደው ለጤና እና ለመብት ጥሰትም በሚዳረጉበት ጊዜ ቢሮው ከአዲስ አበባ ፖሊስ ጋር ተባብሮ ይፋ ባደረገው በ991 ነፃ የስልክ መስመር ባሉበት ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉም ያስገነዝባሉ። ቢሮአቸውም በዚሁ ዙርያ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

‹‹ፍትህ ቢሮ ከእኛ ጋር የሚሰራ መንግስታዊ ተቋም ነው›› የሚሉት ወይዘሮ ሜሮን አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ በተለይ ጥብቅና የሚያስፈልጋቸው፤ የሕግ ክርክር የገጠማቸው፤ መብቶቻቸው የተጣሱ ሴቶች፤ ህፃናትና አካል ጉዳተኞች በመጡ ጊዜ ከአዲስ አበባ ፍትህ ቢሮ ጋር በመሆን መብቶቻቸው እንዲከበር፤ ፍርድ ቤት ላይ ነፃ ውክልና እንዲኖራቸው አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝም ያወሳሉ።

አስተናጋጅ ሴቶች አጭር ቀሚስ እንዲለብሱ የሚገደዱት በሕገወጥ ደላሎች ጭምር በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዞ ቢሯቸው ምን እየሰራ እንደሚገኝ ለጠየቅናቸው ጥያቄም ምላሽ የሰጡን ወይዘሮ ሜሮን "ሕገወጥ ደላሎችን መከታተልና መቆጣጠር የቢሮው ኃላፊነት አይደለም። ሆኖም በዚህ ሂደት ውስጥ ወደ አረብ አገር የሚሄዱ ሴቶች ገንዘባቸውን ያጣሉ። ይታለላሉ። ከዚህም አልፎ ለወሲብ ጥቃት የሚጋለጡበት ሁኔታ አለ። እናም ለእነዚህም ሆነ በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ ሌሎች ሴቶችም መብቶቻቸው እንዳይጣሱ ለማድረግ የሕግ ከለላ ይሰጣል። ከሌሎች ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት ችግሩ እንዲፈታ የማድረግ ሥራም እየሰራ ይገኛል። የተዛባ የሕብረተሰብ አመለካከትን ማስተካከል፤ ሴቷን በትምህርት፤ በኢኮኖሚ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ማብቃትና ማሳተፍ እየሰራቸው ካሉት መካከል ይጠቀሳሉ። ሆኖም የሴቶች ጥያቄ፤ የሴቶች የስርዓተ ጾታ ፍትሃዊነትና እኩልነት ጉዳይ ሴቶች ላይ በሚሰራ መዋቅር ብቻ ይፈታና ጥያቄው ይመለሳል ማለት የዋህነት ነው። የሴቶች ጉዳይ ትልቅ አገራዊ አጀንዳ እንደመሆኑ መጠን፤ የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ በመሆኑም ሊተኮርበት የሚገባ መሆኑን በመግለጽ ሀሳባቸውን አጠናቀዋል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

በሳምንታዊው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በ 1960ዎቹ በተለይም ካለንበት የክረምት ወቅት ጋር ተያይዞ በወቅቱ የተዘገቡ ዜናዎች ምን ይመስሉ እንደነበር ለማስታወስ መርጠናል፡፡ ያለንበት ወቅት ክረምት እንደመሆኑ ወቅቱን ተከትሎ የተከሰቱ አደጋዎችና ሌሎች ጉዳቶችን የዳሰሱ ዘገባዎችን አካተናል፡፡ በመረጥናቸው ዜናዎች ጋዜጣው ዘገባዎችን በተለያዩ የነበሩ ክስተቶችን በማቅረብ ሁሉን አካታች እንደነበርም ያሳየናል፡፡ ከፊሎቹ ዜናዎች በአንድ አንቀፅ ተጠቃለው የዜናን መሠረታዊ ጥያቄዎች ስላላካተቱ ለአንባቢው ጥያቄ ያጭራሉ፡፡ አግራሞትን የሚፈጥሩ አሉ፡፡

### በመብረቅ አደጋ ሁለት ሰዎች ተጐዱ

ዐሰበ ተፈሪ፤(ኢ-ዜ-አ-) በጨርጨር አውራጃ በዋጮ ቀበሌ በዘነመው ኃይለኛ ዝናም ምክንያት የጣለው መብረቅ በ፪ ሰዎች ላይ ጉዳት አደረሰ፡፡ ዕድሜያቸው ፳ ዓመት የሆናቸው አቶ ነጋ አየለ በዚሁ መብረቅ አደጋ ምክንያት ወዲያውኑ ሲሞቱ፤ እንዲሁም ፴ ዓመት ዕድሜ ያላቸው አቶ ዑስማን አደም ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡

(ነሐሴ 8 ቀን 1960 ዓ.ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ድንገተኛ የወንዝ ሙላት የ8 ዓመት ልጅ ወሰደ

መቀለ፤ (ኢ-ዜ-አ-) ታደሰ ገብረ መድህን የተባለ የ፰ ዓመት ልጅ ባለፈው ሰሞን ውቅሮ ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው ወንዝ ውስጥ ገብቶ ሲዋኝ በድንገት ደራሽ ውሃ ደርሶ የወሰደው መሆኑን የትግራይ ጠቅላይ ግዛት ጽ/ቤት ገለጠ፡፡

ይህ አደጋ እንደተሰማ የሟቹ ወላጆች በሥፍራው ደርሰው በሞት የተለያቸውን የልጃቸውን አስከሬን በሕዝብ ርዳታ እንዲወጣ አድርገዋል፡፡

ይህንን የመሳሰሉትን አደጋዎች በሕፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉት ከወላጆች ጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ መሆኑን ጽ/ቤቱ በመጥቀስ በዕድሜ ያልበሰሉ ሕፃናት በክረምት ወራት ወደ ወንዝ እንዳይሄዱ ወላጆች ብርቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስቧል፡፡

(ነሐሴ 8 ቀን 1960 ዓ.ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### በሬው ባለቤቱን ከጅብ አዳነው

(ከአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ)

በጨርጨር አውራጃ ጭሮ ወረዳ ያብዶ ኮሎሎ በተባለው ቀበሌ በአቶ ወጋየሁ ወንድማገኘሁ መሬት ላይ እያረሰ የሚኖር አቶ ሙሳ ቡቲ የተባለ ገበሬ፤ ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳ ዓ/ም ከሌሊቱ ፳ ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በአንደኛው ቤት ውስጥ ካሉት ከብቶች መካከል አንዲት ፍየል ጅብ ጐትቶ ሲያወጣት ባለቤቱ ነቅቶ ጅቡን ሲከላከል ሆዱን ነከሰው፣ ሰውየውም የጅቡን አፍንጫውንና አገጩን አፍኖ ሲይዘው ሆዱን ለቆ የቀኝ ባቱን ነክሶ ፲፰ ሜትር ያህል ጐትቶ ሊበላው ሲተናነቅ የጥቁር ጋርማ ጐባ በሬ እውጭ ከታሠረበት ገመዱን በጥሶ ጅቡን ተከታትሎ በማባረር ባለቤቱን ከመበላት ያተረፈው መሆኑንና ሰውየውም በልዑል ሣህለ ሥላሴ ሆስፒታል ታክሞ የዳነ መሆኑን አቶ ወጋየሁ አስረድተውናል፡፡

(ሐምሌ 7 ቀን 1960 የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ኃይለኛ ዝናም ፲፪ ቤቶችን አፈረሰ

አዋሳ (ኢ-ዜ-አ-) በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት በአዋሳ ከተማ ሰኔ ፫ ቀን ፳ ዓ/ም/ ነፋስ አስከትሎ የጣለው ኃይለኛ ዝናም ፲፪ ቤቶች አፈረሰ ፡፡ በዚሁ ቀን ዝናሙ የዘነመው ከቀኑ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ፩ ሰዓት ነበር፡፡

ይኸው ኃይለኛ ዝናምና ነፋስ የቤቶቹን ክዳን ቆርቆሮውን ገነጣጥሎ በመጣል በባለንብረቶቹ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ከማድረሱም በላይ ፤ በአንዳንድ ሥፍራዎችም የስልክ ሽቦዎችን ቆራርጧል፡፡

ከዚህም ሌላ ዛፎችን ከሥራቸው ነቃቅሎ የጣለ ሲሆን ፤በሰው ሕይወትና በእንስሳት ላይ ግን የደረሰ አደጋ አለመኖሩን የጠቅላይ ግዛቱ ፖሊስ የወንጀል መከላከልና ምርመራ ረዳት ዋና አዛዥ ኰሎኔል አየለ ወልደ ሥላሴ ገልጠዋል፡፡

(ሰኔ 13 ቀን 1960 የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ባለ አንድ እግሯ ፍየል በሕይወት ትገኛለች

ዓድዋ (ኢ-ዜ-አ-) ባለፈው ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. የተወለደችው ባለ አንድ እግር የፍየል ግልገል እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወት ትገኛች፡፡ ግልገሏ የአቶ በሪሁን ምራጭ ንብረት ናት፡፡

ይህችው አስገራሚ ፍጥረት የተወለደችው በዓድዋ አውራጃ ግዛት በዓዲ አበና ወረዳ በእንዳማሪያም ሽዊት ቀበሌ መሆኑን የአውራጃው ጽሕፈት ገለጠ፡፡

(ነሐሴ 8 ቀን 1960 ዓ.ም የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ፫ ሺ ፫ መቶ ጅቦችና ቀበሮዎች ተገደሉ

መቀሌ፤(ኢ-ዜ-አ-) በትግሬ ጠቅላይ ግዛት በራያና አዘቦ አውራጃ ግዛት በበረሀሌና በጸሎም ወረዳ ውስጥ ፪ ሺ ፬፻፺፩ ጅቦችና ፳፻፸፬ ቀበሮች መገደላቸውን የትግራይ ልማት ድርጅት የመንገድ ሥራ አላፊ አቶ ገብረክርስቶስ ገብረ እግዚአብሔር ገለጡ፡፡

አቶ ገብረ ክርስቶስ እንደገለጡት ልዑል ራስ ሥዩም ተገኝተው የሽዊትንና የጨርጨር ወረዳ ግዛቶች በጐበኙበት ወቅት በአገሩ ላይ የጅብና የቀበሮ መንጋ ተነሥቶ በሰውና በእንስሳ ላይ ጉዳት ማድረሱን ሕዝቡ ባቀረበው አቤቱታ መሠረት ሁኔታውን ከመረመሩ በኋላ ፤ የጅብና የቀበሮው መንጋ በየጊዜው እንዲጠፋ ካልተደረገ ወደፊት ከፍ ያለ ጉዳት እንደሚያስከትል በመገንዘብ፤ ጉዳዩ ከሚመለከተው መሥሪያ ቤት ጋር ተነጋግረው ባስፈቀዱት መሠረት ፤በትግራይ ልማት ድርጅት አማካይነት የሚመረጡ በየወረዳዎቹ ተቋቁሞ በተደረገው ዘመቻ ከላይ የተጠቀሱት አውሬዎች በመድኃኒት ርዳታ ተገድለዋል፡፡

(ሰኔ 12 ቀን 1960 የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

ለመጀመሪያ ጊዜ

### በኢትዮጵያ የተሠራ የጣሳ ሥጋ ወደ እንግሊዝ ይላካል

ድሬዳዋ ፤(ኢ-ዜ-አ-) ቻንድረስ አፍሪካ የተባለው የሥጋ ፋብሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የታሸገ ሥጋ ወደ እንግሊዝ አገር ሊልክ ነው፡፡

ድሬዳዋ ከተማ ያለው ይህ የሥጋ ፋብሪካ ከእንግሊዝ ወታራዊ ድርጅት ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት፤ በጣሳ የታሸገ የኢትዮጵያ የቀንድ ከብቶች ውጤት በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደዚህ አገር ይሰድዳል፡፡

በኢትዮጵያ የተሠራው የታሸገ ሥጋ በውጪ አገር ዘንድ በጣም ተፈላጊነት ያለውና ከሌሎች የዓለም ሥጋ ፋብሪካዎች የሚወዳደር መሆኑን የሥጋው ፋብሪካ አላፊ ገለጡ፡፡

አሁን ወደ እንግሊዝ አገር የሚሄደው የታሸገ ሥጋ፤ በቻንድራ ፋብሪካ ገና ተሠርቶ ያላለቀ ሲሆን ፤ከሥር ከሥሩ ወደዚሁ አገር እንደሚላክ አላፊው ሲገልጡ፤ ምን ያህል ጣሳ ሥጋ እንደሚላክ ለመጥቀስ አልፈቀዱም፡፡

ይሁን እንጂ ብዛት ከፍ ያለ ሥጋ በልዩ ቅመም ተቀምሞ ወደ እንግሊዝ አገር የሚላክ መሆኑ ተገምቷል፡፡

(ሰኔ 2 ቀን 1960 የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

# ዓለም አቀፍ




## በኒውክሌር ጣቢያ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጥቃት ራስን የማጥፋት ድርጊት ነው

የኒውክሌር ግጭት ስጋት ከብዙ አሥርት ዓመታት በኋላ ዳግም መመለሱን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ተናገሩ፡፡ ኒውክሌር የታጠቁ ሀገራት መንግሥታትም የጦር መሣሪያውን ቀዳሚ ምርጫቸው እንዳያደርጉም ጠይቀዋል።

በዩክሬን "ዛፖሪዝዢያ" በሚባለው የኒኩሌር ጣቢያ ላይ የተኩስ ልውውጦች መደረጋቸውን የገለፁት ዋና ፀሐፊው፥ በኒውክሌር ጣቢያ ላይ የሚደርሰው ማንኛውም ጥቃት ራስን የማጥፋት ድርጊት ነው ሲሉ በጃፓን ቶኪዮ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ተናግረዋል፡፡

የዩክሬን ኃይሎች በሀገሪቱ ደቡባዊ ዛፖሮዢ ክልል የሚገኘውን የኒውክሌር ጣቢያን ባለፈው አርብ ጥቃት ፈፅመዋል ስትል ሞስኮ መክሰሷን ተከትሎ፥ ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በአውሮፓ ትልቁ የኒውክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የኒውክሌር አደጋ አሳሳቢነት ገልፀዋል፡፡ ኪየቭ በበኩሏ ሩሲያ ተቋሙን ለወታደሮቿ እንደ ጋሻ እየተጠቀመች ነው ስትል ትከሳለች።

ጉቴሬዝ በቶኪዮ ሁለቱንም ወገኖች ሳይወቅሱ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፥ በኒውክሌር ጣቢያ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጥቃት ራስን የማጥፋት ድርጊት መሆኑን ተናግረዋል።

ዋና ፀሐፊው ጥቃቶች እንደሚቆሙ እና በተመሳሳይ ጊዜ ዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኃይል ኤጀንሲ በጣቢያው አደጋን ማስቀረት የሚያስችል ቅኝት እንደሚያደርግ ተስፋ አደርጋለሁ ነው ያሉት።

ዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ በዛፖሮዢ የኑክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ላይ የደረሰው ድብደባ "በጣም አሳስቦኛል" ማለቱን የሲ ጂ ቲ ኤን እና አር ቲ ዘገባዎች ማመልከታቸውን ጠቅሶ ኤፍቢሲ ዘግቧል።

## በጋዛ ሰርጥ በግብጽ አሸማጋይነት የተደረሰው የተኩስ አቁም ተግባራዊ ሆነ



ለሦስት ቀናት በዘለቀውና ቢያንስ 43 ሰዎች የሞቱበትን ግጭት ተከትሎ በእስራኤል እና በፍልስጤም ታጣቂዎች መካከል የተኩስ አቁም ስምምነት ተግባራዊ ሆነ። በግብጽ አሸማጋይነት የተደረሰው ስምምነት ከትናንት ወዲያ ከእኩለ ለሊት ጀምሮ ተግባራዊ መደረጉን የፍልስጤም እስላማዊ ጂሃድ (ፒአይጄ) ተናግረዋል።

የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ያይር ላፒድ ጽህፈት ቤት የተኩስ አቁም መደረጉን አረጋግጧል። የሰሞኑ ግጭት እአአ 2021 ለ11 ቀናት ከዘለቀው ግጭት በኋላ በእስራኤል እና በጋዛ መካከል ከተፈጠረው ከባዱ ነው ተብሏል። ስምምነቱ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ለተተኮሱ ሮኬቶች ምላሽ ነው በሚል የእስራኤል ወታደራዊ ኃይል በጋዛ የእስልምና ጂሃድ ዒላማዎችን እየመታ መሆኑን አረጋግጧል። የአገሪቱ መገናኛ ብዙሃን ከስምምነቱ መተግበር በኋላ ከጋዛ የተወሰኑ ሮኬቶች መተኮሳቸውን ዘግበዋል።

ኋላም የተኩስ አቁም ስምምነቱ ተግባራዊ እየሆነ ይመስላል። በታጣቂ ቡድን ለተፈጠረው ስጋት የእስራኤል ጦር በጋዛ ሰርጥ በሚገኙ ቦታዎች ላይ የአጸፋ ምላሽ መስጠት መጀመሩን ገልጾ ነበር። ይህም እስራኤል በዌስት ባንክ ከፍተኛ የፒአይጄ አባል በቁጥጥር ስር ካዋለች በኋላ የተፈጠረውን ውጥረት ተከትሎ የተከሰተ ነበር።

እሑድ ማምሻውን የፍልስጤም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው ሕይወታቸው ካለፉት 43 ሰዎች መካከል 15ቱ ሕጻናት መሆናቸውን መረጋገጡን አስታውቋል። የጋዛ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለፍልስጤማውያን ሞት እና ከ300 በላይ ለሚሆኑት ሰዎች መቁሰል "የእስራኤል ጥቃትን" ተጠያቂ አድርጓል።

የፒአይጄ አዛዥ ሁለተኛ ሰው የሆነው ካሊድ መንሱርን ጨምሮ በእስራኤል ጥቃት የተገደሉትን የቀብር ሥነ-ሥርዓት ለማከናወን እሑድ ዕለት ከፍተኛ ሕዝብ ተሰብስቧል። የጤና ባለሥልጣናት ሆስፒታሎች ለተጨማሪ ሁለት ቀናት ጄነሬተሮችን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ነዳጅ ብቻ እንዳላቸው ማስጠንቀቃቸውን እና በጋዛ የሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረስ ያለው ስጋት ከተገለጸ በኋላ ነው የተኩስ አቁም ስምምነቱ የተደረሰው።

የእስልምና ጂሃድ ቃል አቀባይ ታሪቅ ሰልሚ "እስራኤል በሕዝባችን ላይ የምታደርሰውን ጥቃት ለማስቆም በግልጽ የተደረገውን ጥረት እናደንቃለን" ብለዋል። እስራኤል የተኩስ አቁም ስምምነቱ ከተጣሰ "ጠንካራ ምላሽ የመስጠት መብቴን እጠቀማለሁ" ብላለች። በጋዛ ከደረሰው ሞት የተወሰነው የተፈጸመው በፒአይጄ ታጣቂዎች ነው ስትል እስራኤል ትከሳለች።

የሰሞኑ ግጭት የተቀሰቀሰው እስራኤል የፒአይጄ ኃላፊ እንደሆነ የሚነገርለትን ባሴም ሳዲን ሰኞ ምሽት ዌስት ባንክ ውስጥ በቁጥጥር ስር ማዋሏን ተከትሎ ነው። በእስራኤላውያን አረቦች እና በፍልስጤማውያን ጥቃት 17 እስራኤላውያን እና ሁለት ዩክሬናውያን ሕይወታቸውን ካጡ በኋላ ነው የእስር ዘመቻው በጄኒን አካባቢ የተጀመረው።

በጋዛ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱት ጠንካራ ታጣቂ ቡድኖች አንዱ ፒአይጄ ነው። ቡድኑ በኢራን የሚደገፍ ሲሆን ዋና መስሪያ ቤቱን በሶሪያ ርዕሰ መዲና ደማስቆ ይገኛል። በእስራኤል ላይ ሮኬት ማስወንጨፍን ጨምሮ ለበርካታ ጥቃቶች ተጠያቂ ነው። እአአ 2019 እስራኤል ላይ ጥቃት ለመፈጸም አቅዶ ነበር ያለችውን የፒአይጄን አዛዥ መግደሏን ተከትሎ በእስራኤል እና በቡድኑ መካከል ለአምስት ቀናት የዘለቀ ግጭት ተካሂዷል።

በግጭቱ 34 ፍልስጤማውያን ሲሞቱ 111 ቆስለዋል። 63 እስራኤላውያን ደግሞ የሕክምና ድጋፍ አስፈልጓቸዋል። ከተገደሉት ፍልስጤማውያን መካከል ሮኬቶችን ለማስወንጨፍ በዝግጅት ላይ የነበሩትን ጨምሮ 25 ያህሉ ታጣቂዎች ናቸው ስትል እስራኤል መግለጿን ቢቢሲ ዘግቧል።

# የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 001/2015

የጉለሌ ክ/ከተማ የወረዳ 02 ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ለ2015 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች ማለትም

1- ሎት 01 የአላቂ የቢሮ ዕቃዎች
2- ሎት02/ የጽዳት ዕቃዎች
3- ሎት 03/ የደንብ ልብስ ዕቃዎች የደንብ ልብስ ስፌት
4- ሎት 04/ የህትመት ስራ የትራንስፖርት መስተንግዶ እና የኤሌክትሮኒክስ ጥገና እና የአዳራሽ ዲኮር
5- ሎት05/ የመኪና ጎማና ባትሪ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል በመሆኑም በጨረታው መካፈል የሚፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን ሁኔታዎች በቅድሚያ ማሟላት ይኖርባቸዋል

-ተጫራቾች በተሰማሩበት የስራ መስክ የዘመኑን ግብር ለመክፈላቸው እና የታደሰ የንግድ ፍቃድ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል

- ተጫራቾች በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ከሆነ የሚወዳደሩት በሚያመረቱት እቃ ወይም ተጨማሪ እሴት ለጨመሩት እቃ ሲሆን ከዚህ ውጪ ለሆኑ እቃዎች የሚወዳደሩት እነደማንኛውም ተጫራች ሰነድ በመግዛት ይሆናል :: ተወዳዳሪዎች በሚያመርቱት እቃ ሲወዳደሩ እና ካደራጃቸው መስሪያ ቤት የድጋፍ ወረቀት ሲያመጡ ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል ::
- የመንግስት የግዥ ጨረታ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል የተሟላ ማስረጃ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል ::
- ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው::
- የጨረታ ሰነዱን በጉለሌ ክ/ከተማ ከወረዳ 02 ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት 4ኛ ፎቅ ላይ ቢሮ ቁጥር 14 በመምጣት ሰነዱን የማይመለስ በብር 100 ( አንድ መቶ ብር) በመግዛት መውሰድ ይኖርባቸዋል
- የጨረታውን ሰነድ ኦርጅናል እና ኮፒ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው::
- ጨረታው ጋዜጣ ከወጣበት ቀናት አንስቶ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ይቆያል
- ጨረታው በአስረኛው ቀን 11፡10 ላይ ታሽጎ በአስራ አንደኛው ቀን 3:30 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት 4ኛ ፎቅ ላይ ቢሮ ቁጥር 14 ይከፈታል
- ተጫራቾች ከጨረታው ሰነድ ውጪ ተሞልቶ የመጡት ሰነድ ተቀባይነት የለውም
- መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው
- ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ የሚኖርባቸው ሲሆን ይኸውም
- ሎት 01/ የአላቂ የቢሮ ዕቃዎች የሚሆን ብር 5000ብር (አምስት ሺህ ብር) ማስያዝ ይኖርባቸዋል
- ሎት02/ የጽዳት ዕቃዎች የሚሆን ብር 6500ብር (ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ማስያዝ ይኖርባቸዋል
- ሎት 03/ የደንብ ልብስ ዕቃዎች የደንብ ልብስ ስፌት የሚሆን ብር 3500ብር (ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ማስያዝ ይኖርባቸዋል
- ሎት 04/ የህትመት ስራ የትራንስፖርት መስተንግዶ እና የኤሌክትሮኒክስ ጥገና እና የአዳራሽ ዲኮር የሚሆን ብር 5000ብር (አምስት ሺህ ብር) እና
- ሎት05/የመኪና ጎማ እና ባትሪ የሚሆን ብር 5000 ብር (አምስት ሺህ ብር) ማስያዝ ይኖርባቸዋል እንዲሁም የጨረታ አሸናፊ ከሆኑ በኋላ የውል ማስከበሪያ 10% ማስያዝ ይኖርባቸዋል
- ተጫራቾች ናሙና ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ናሙና የማቅረብ ግደታ ይኖርባቸዋል የሚቀርቡትም ናሙናዎች ተፈትተው የሚታዩ መሆናቸውን ተጫራቾች ማወቅ አለባቸው ::
- ተጫራቾች የአሸነፉባቸውን ዕቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል :
- መ/ቤቱ ከአሸናፊው ድርጅት የአሸነፉበትን ዋጋ መጠን እና ብዛት 25% ተጨማሪ ትዕዛዝ መጠየቅ የሚችል መሆኑ መታወቅ አለበት ::
- መ/ቤቱ ከውል በፊት እንደአስፈላጊነቱ የእቃውን ብዛት 20% መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚችል መታወቅ አለበት

ለተጨማሪ ማብራሪያ
አድራሻ - ስድስት ኪሎ ከፍ ብሎ ስብሰባ ማዕከል አጠገብ ወደ ህምሌ 19 መናፈሻ 100 ሜትር ገባ ብሎ
ስልክ ቁጥር፡- 011-1-23-44-23 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ

**የጉለሌ ክ/ከተማ የወረዳ 02 ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት**

# የልዩ ልዩ እቃዎች የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ
# የጨረታ ቁጥር 03/2014

ሆራይዘን አዲስ ጎማ ማ/ኃላ/የተ/የግ/ማ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ልዩ ልዩ ዕቃዎች

1. የብረት በርሚል
2. ካሳ ተከፈለባቸው ጐማዎች ያገለገሉ ብላደሮች
3. ልዩ ልዩ ዕቃዎች
4. ያገለገለ ዘይት፤ የፈርነስ ፍሳሽ
5. ልዩ ልዩ የኮርድ ክሮች
6. ልዩ ልዩ ስኮርች ኮምፓውንዶች
7. ስክራፕ እና አገልግሎት ሰጥተው የተመለሱ የተቆረጡ ጎማዎች በመሆኑም ፍላጎት ያላቸውን ተጫራቾች በሙሉ እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡

**በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡**

1. ተጫራቾች ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ 21 ቀን 2014 ዓም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ በሥራ ቀናት የማይመለስ ብር 150.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ብር/ በመክፈል ከኩባንያው የምርት ሽያጭ ቢሮ መግዛት እና እቃዎቹን ማየት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች መግዛት የሚፈልጓቸውን እቃዎች በዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ የእያንዳንዱን ዋጋ በግልፅ ሞልተው፤ ሙሉ ስማቸውን ጽፈው ከፈረሙበት በኋላ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት እለት ጀምሮ እስከ ነሐሴ 21 ቀን 2014 ዓም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ በሽያጭ ቢሮ ፊት ለፊት ባለው የጥበቃ በር ቁጥር 2 ቢሮ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡ የጨረታ ሣጥኑ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 4፡05 ሰዓት ይታሸጋል፡ ፡ ጨረታው ነሐሴ 21 ቀን 2014 ዓም ከጠዋቱ 4፡20 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልጽ ይከፈታል፡፡
4. ድርጅቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡-- ንብረት አስተዳደር መምሪያ ቢሮ
ስልክ ቁጥር 011-442-15-55/249 ወይም 0943880372 መጠየቅ ይቻላል፡

**ሆራይዘን አዲስ ጎማ ማ/ኃላ/የተ/የግ/ማ**

# የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
# የግዥው መለያ ቁጥር 001/2015

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት ፑል በፑል አስተዳደሩ ስር ለሚገኙ ጽ/ቤቶች ለ2015 በጀት አመት የሚያስፈልጋቸውን ሎት 1 አላቂ የቢሮ እቃዎች ፣ ሎት 2 ቋሚ የቢሮ እቃዎች /ፈርኒቸር/ ግዥ ፤ ሎት 3 ኤሌክትሮኒክስ የቢሮ እቃዎች ግዥ ፣ ሎት 4 የጽዳት እቃዎች ፣ ሎት 5 የደንብ ልብስ ግዥ ፣ ሎት 6 የህዝብ አውቶቢስ አገልግሎት ክራይ ግዥ ፣ ሎት 7 ታክሲና አይሱዙ ክራይ አገ/ት ግዥ ፣ ፤ ሎት 8 ኤሌክትሮኒክስ የቢሮ እቃዎች ጥገና ግዥ ፣ ሎት 9 የጉልበት ስራተኛ አገት ግዥ ፣ ሎት 10 የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ፣ ሎት 11 የህትመት ውጤቶች አገ/ት ግዥ ሲሆኑ ብቃት ያላቸውንና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈጸም ይፈልጋል በዚህም መሰረት ፡

1) በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ እና ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ ፣ የቲን እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ፤ በአቅራቢነት የተመዘገቡና በአቅራቢነት ስለመመዝገባቸው የሚያስረዳ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ እንዲሁም ለታክሲ ክራይ አገ/ት እና የህዝብ አውቶቡስ አገ/ት ለማቅረብ የሚወዳደሩ ተወዳዳሪዎች በስማቸው የተመዘገበ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ::
2) ተጫራቾች የጨረታውን ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ለሎት 1 አላቂ የቢሮ እቃዎች ግዥ ብር 10,000 ፣ ሎት 2 ቋሚ የቢሮ እቃዎች /ፈርኒቸር / ግዥ ብር 300,000 ፣ ሎት 3 ኤሌክትሮኒክስ የቢሮ እቃዎች ግዥ ብር 30,000 ፣ ሎት 4 የጽዳት እቃዎች ብር 5,000፣ ሎት 5 የደንብ ልብስ ግዥ ብር 5,000፣ ሎት 6 የህዝብ አውቶቢስ አገልግሎት ክራይ ግዥ ብር 5,000 ፣ ሎት 7 ታክሲና አይሱዙ ክራይ አገ/ት ግዥ ብር 5,000፣ ሎት 8 ኤሌክትሮኒክስ የቢሮ እቃዎች ጥገና ግዥ ብር 10,000 ፣ ሎት 9 የጉልበት ሰራተኛ አገ/ት/ ግዥ ብር 5,000 ፣ ሎት 10 የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 5,000 ፣ ሎት 11 የህትመት ውጤቶች አገ/ት ግዥ ብር 10,000 ማስያዝ ያለባቸው ሲሆን የጨረታ ማስከበሪያውን ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው ::
3) ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት እለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 100(አንድ መቶ) በመክፈል 5ተኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት በመንግስት ግዥ ቡድን ቢሮ ቁጥር 02 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ ::
4) ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን ኦሪጂናልና ኮፒ ሰነዶችን ለየብቻው በታሸገ ኤንቨሎፕ በማደራጀት ማስታወቂያው ከወጣበት እለት ጀምሮ በ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የክፍለ ከተማው ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት በሚገኝበት ሀይሌ ጋርመንት አደባባይ በሚገኘው የአስተዳደሩ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ላይ ቢሮ ቁጥር 02 በመቅረብ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5) ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአስረኛው ቀን በ11፡30 ሰአት ታሽጎ በማግስቱ በ11ኛው ቀን 4፡30 ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት በመንግስት ግዥ ቡድን ቢሮ ቁጥር 02 ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበአል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰአት ታሽጎ ይከፈታል ፡፡
6) ተጫራቾች ጨረታው አስቸኳይ ስለሆነ የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ለሎት 1፣2፣3፣4፣5 እና 11 ናሙና ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን ሌሎች ናሙና ያልተጠየቀባቸው ሎቶች ሎት 6፣7፣8፣9 እና 10 ግን በቀረበው የፍላጎት መግለጫ መሰረት የተሟላ የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጅትና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ፡፡
7) ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ወይም የአገልግሎት ግዥ ለያንዳንዱ እቃ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል
8) የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም ፡፡
9) አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈጻሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ፡፡
10) መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው በተጨማሪ ለማብራሪያ ጥያቄ ::

**አድራሻ** ሀይሌ ጋርመንት ላፍቶ አደባባይ በሚገኘው የአስተዳደሩ ህንፃ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 02 የን/ስ/ላ ክፍለ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ ቡድን ስልክ ቁጥር – 0118-83-80-20

**በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ ቡድን**